


ሉሉ ታደሰ በድሬዳዋ አካባቢ በደርግ ነፈሰገዳዮች በ1970 ዎቹ ከተገደሉት የኢሕአፓ ከዋከብት አንዱ ነበር

# ኢትዮጵያ

የካቲት/መጋቢት 2007 3ኛ ዓመት

ርእስ አንቀጽ ገፅ 2
የቀረን አንድ ምርጫ - የተባበረ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ
//
ገፅ 3
ዜና ከተባለ
ምን ይሰማ....... አገር
//
ዜናዎች ገፅ 4
//
ትናንትና ገፅ 5
//
ዴሞክራሲያ ገፅ 6
//
ትናንትና ገፅ 10
እንጻፍ ካልንማ--3

የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

EPRP.COM
ASSIMBA.ORG
DEBTERAW.COM
ETHIOLION.COM
ወዘተ.

- FACE BOOK (ethiopianewspape

## ሽፈራው ተ/ማሪያም ሙስሊሙ ላይ ዛተ

ወያኔ ፤ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ እና ይበልጥ እያስፈራው ስለመጣ ፤ ሙስሊሞቹ የሚያደርጉትን ትግል በሀይል ለመቀልበስ አዲስ የማስፈራራት ዘመቻ ጀመረ፡፡

የማስፈራራቱን ዘመቻ በዋናነት እንዲመራው የተደረገው ፤ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ሺፈራው ተ/ማሪያም ሲሆን ፤ የጸጥታ እና የደህንነት ሀላፊው ተስፋዬ ዲዳ የተባለው ደግሞ ዘመቻውን እንዲአስፈጽም ሀላፊነት የወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ፤ የካቲት 23 ፤ ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ በኮልፌ ቀራኒዮ ፤ ሕዝበ ሙስሊሙን በመሰብሰብ ፤ <<ከዚህ በኋላ ምንም አይነት ተቃውሞ ብታደርጉ የሚወሰደው እርምጃ ከባድ ይሆናል...ተቃውሞውን የሚያደራጁትን መሪዎች ማጋለጥ አለባችሁ...>> እያሉ ለማስፈራራት ቢጥሩም ፤ የተሰበሰበው ሙስሊም ግን ዛቻና ማስጠንቀቂያውን እንደተለመደው በዝምታ ተቃውሞ አልፎታል፡፡

ሽፈራው ተ/ማሪያም ፤ በሙስሊሙ ጉዳይ ከወያኔ በኩል ጠንከር ያለ ትችት ስለደረሰበት ፤ በሕዝበ ሙስሊሙ ላይ ከባድ እርምጃ እወስዳለሁ ይበል እንጂ ፤ ከዚህ በፊት ለተቃውሞ በወጡ ሰላማዊ ሙስሊሞች ላይ ድብደባ ፤ እስር እና ግድያ ፈጽሞ ትግላቸውን ለማቆም አለመቻሉ የሚታወስ ነው፡፡

## የወያኔ ሰላይ ከሆላንድ ተባረረ

ወያኔ ፤ በስለላ ሥራ ያሰማራው እና አለማየሁ ስንታየሁ በሚል የስደተኛ ስሙ የሚታወቅ እውነተኛ ስሙ ግን ዘለቀ ፎላ የተባለ ግለሰብ ፤ ሰላይ መሆኑ በመረጋገጡ ፤ ከሆላንደ መባረሩን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ማስታወቃቸውን የደረሰን ሪፖርት ያስረዳል፡፡

ዘለቀ ፎላ ፤ በደርግ የአገዛዝ ዘመን ወታደር የነበረና ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ደግሞ ለወያኔ ያደረ ሲሆን ፤ ወያኔ ፤ ዘለቀ ፎላ ለሰጠው አገልግሎት ወሮታ በማለት ስሙን በመቀየር ወደ ሆላንድ የላከው እና የሆላንድን የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ በስደተኝነት ተመዝግቦ የሚኖር ግለሰብ ነበር፡፡

ይሁንና ፤ በሆላንድ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በስለላ ተግባር የተሰማራ መሆኑን በተመለከተ ክስ በመመስረታቸው የተነሳ ፤ የሆላንድ መንግሥት ሁኔታውን ካጣራ በኋላ ፤ ሆላንድን በአስቸኳይ ለቆ እንዲወጣ እና ዳግመኛም የሆላንድን መሬት እንዳይረግጥ በሚል ውሳኔ ከሀገር አባሮታል፡፡

በሆላንድ የሚገኙ የወያኔ አባላት እና አገልጋዮቹ ፤ ዘለቀ ፎላን የማስቀረት ወይም እየተመላለሰ ቤተሰቦቹን እንዲጠይቅ በሚል የፊርማ ማሰባሰብ ለማድረግ ቢጥሩም ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡

## የወያኔ ቴሌቪዥን ታገደ

የወያኔ ቴሌቪዥን ፤ ዮ.ቲዩብ (youtube) ከተባለው እና በዓለም ላይ እጅግ ግዙፍ በሆነው ማህበራዊ ሚዲያ እንዳይተላለፍ ታገደ፡፡ እገዳው የደረሰበት ፤ በዩ. ቲዩብ ማህበራዊ ሚዲያ የቪዲዮ ቅጂዎችን መብት (copyright) በመጣስ የራሱን ቅጂዎች ሲያስተላልፍ በመገኘቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በፊት ፤ ይኸው የወያኔ ቴሌቪዥን ፤ ከዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን (FIFA) እና ከአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን (CAF) እውቅና ውጭ ፤ የእግር ኳስ ወድድሮችን የማስታወቂያ ዋጋ እያስከፈለ ሲያስተላልፍ በመገኘቱ ፤ ከፍተኛ ውግዘትና ተቃውሞ ገጥሞት እንደነበር አይዘነጋም፡፡

## የአቡነ መርቆሬዎስ 25ኛ በዓለ ሲመት ይከበራል

በስደት የሚገኘው ህጋዊው ሲኖዶስ ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ መርቆሬዎስን 25ኛ በዓለ ሲመትን ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ አዳራሽ ውስጥ እንደሚያከብር የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት አስታወቀ፡፡

ቅዳሜ ሚያዚያ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ከሚደረገው በዓለ ሲመት በተጨማሪ ፤ ሜሪላንድ ውስጥ የተገዛውን የመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤትን አስመልክቶ የምረቃ ሥነ-ስርዓት እንደሚኖርም ታውቋል፡፡ በዚህ ታሪካዊ በዓል ላይ ፤ ከአሜሪካና ከመላው ዓለም የሚመጡ የሀይማኖት አባቶች የሚገኙ ሲሆን ፤ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ መዝሙሮች ፤ ድራማዎች ፤ የቅዱስነታቸው ቡራኬ ከመድረኩ የሚቀርቡ ሲሆን ፤ እንዲሁም እሳቸውን አስመልክቶ የክብር እንግዶች ንግግር እንደሚያደርጉ ስለ በዓለ ሲመቱ የተያዘው የጊዜ ሰሌዳ ያስረዳል፡፡

## ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

በኢትዮጵያና በጎረቤት አገሮች ለሚገኙ አድማጮቹ ከመጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም (April 1, 2015) ፕሮግራሙን በሳተላይት አማካይነት ማሰራጨት የሚጀምር መሆኑን በደስታ እንገልጻለን፡፡



# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ
5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

### የቀረን አንድ ምርጫ - የተባበረ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ /

ወያኔ ፍጹም ጸረ - ኢትዮጵያና ጸረ - ሕዝብ የሆነ ቡድን መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል ። ዐይን ባወጣ ፈላጭ ቆራጭነት ከሥልጣኑ መንበር ተቆናጥጦ ባሳለፋቸዉ ሀያ ሰስት ዓመታት ዉስጥም ከዚህ ወዲያ የታዘብነዉ የለም ። ቀድሞዉኑ ቢሆን በተፈጥሮዉ ጠባብና ጸረ ሀገር ከሆነና በዉስጠ ድርጅታዊ ሕይወቱ በእኩይ ሤራዎች በተተበተቡ የፖለቲካ ግድያዎች ከጨፈገገ ወያኔን ከመሰለ ዝግ ቡድን ለዜጎች ዘለቄታ ያለዉ ብሔራዊ ክብርንና ብልጽግናን የሚያጎናጽፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መጠበቁ ተላላነት አልነበረም አይባልም ። ይሁንና ፤ እንደ የዋሃኑ ፖለቲከኞቻችን እምነት ወያኔ በመዋል በማደር የሚታረም ሳይሆን ፤ ገና በጫካ ዘመኑ ታገልኩላቸዉ ከሚላቸዉ አዉዳሚ መርህ ግብሮች ንቅንቅ ከሚል ኢትዮጵያም ሆነች ከኢትዮጵያዊነት ጋር አጣምረን የምናስባቸዉ ዕሴቶች ተያይዘዉ ዉድም ቢሉ የሚመርጥ ኃይል መሆኑን በገሃድ አረጋግጧል ።

በየትኛዉም ማዕዘን ብናነጻጽረዉ በዛሬይቱ ኢትዮጵያችን የመልካም አስተዳደርም ሆነ የዴሞክራሲ ደብዛ የለም ። በምትኩ በዘር ሐረግ የተሳሰሩ የጎሳ ፖለቲካ አቀንቃኞች በፈላጭ ቆራጭነት ተሰይመዉ ራሳቸዉን ሕግ ያደረጉበት፤ እንዳሻቸዉ የሀገር ሀብት የሚዘርፉበትና የሚፈነጩበት ፍጹም አምባገነናዊ ጽልመት ሰፍኗል ።በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ዉስጥ የረበበዉ እዉነታ በሙሉ አያዎ የቀነበበዉ ነዉ ። -- ሕገ መንግሥት አለ ፤ ነገር ግን ከረቂቅ እስከ ሕትመት ከፈሰሰበት የገንዘብ ወጪ አኳያ ሲመዘን በጣም የረከሰ የወያኔን ፈቃድና ድርጅታዊ መመሪያዎች ብቻ በሥራ ማስተርጎሚያ መሣሪያ ነዉ ። ፍርድ ቤቶች አሉ ፤ ሆኖም ነጻነት የሌላቸዉ የአገዛዙን ተቀናቃኞች ለማነቅ ወይም ለመኮድኮድ ተዘጋጅተዉ የተዘረጉ እጆች ናቸዉ ። ጋዜጦች አሉ ፤ ነጻ አዘጋጆቻቸዉና ጋዜጠኞቹ ግና ተሰድደዋል ወይም ዘብጢያ ተከርችመዋል ። ( በጠራራ ጸሀይ በገዠራ የተፈለጡ ተስፋዬ ታደሰን የመሳሰሉ ጋዜጠኞችም መኖራቸዉ እንዳይዘነጋ ።) በየዓመቱ የሚመዘገበዉ የመዋዕለ ንዋይ ዕድገት በሽበሽ መሆኑም ነጋ ጠባ እየተለፈፈ ነዉ ፤ በረሀብ የሚንጠራወዙትን ዜጎች ግን ቤቱ ይቁጠራቸዉ ።

ፖለቲካዉ ከሚዘወርበት ሥርዓት አንጻር ወያኔ መድብለ ድርጅታዊነትን ከለፈፈ ከራርሟል ። ዕዉነታው ግን በአፋራሹ መሆኑን ደጋግመን ያየነዉ ነዉ ። ወያኔ ሀገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች ሠርጎ መግባቱና ባሻዉ ጊዜም ህጋዊነታቸዉን እንደሚገፍፋቸዉ በቅርቡ በአንድነትና በመኢአድ ላይ የወሰዳቸዉ ርምጃዎች ያረጋግጡልናል ። ተቃዋሚ የፖለቲካ ስብስቦች አስፈላጊነታቸዉ ወያኔያዊዉን የፌዝ ምርጫ ከማዳመቂያ ያለፈ አይደለም ። እስካዛሬ ድረስ በተደረጉት የይስሙላ ምርጫዎች ባደረጉት ተሳትፎ ወያኔ የሚፈልገዉን የህጋዊነት ካባ ከማልበስና ሕዝባችን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለዉን ህልም መዘባበቻ ከማድረግ ወዲያ ያተረፉት የለምና ሀቀኛነቱ ያላቸዉ ድርጅቶች ቆም ብለዉ ለወደፊቱ መከተል የሚኖርባቸዉን የትግል ስልት ከወዲሁ መተለም ይገባቸዋል ። ከእንግዲህ ከምርጫ ቦርድም ሆነ ከአሻንጉሊቶቹ ፍርድ ቤቶች ጋር የሚደረገዉ መጯጯህ የሚፈይደዉ ነገር የለም ። ከተግባር መማር ደግሞ ብልህነት ነዉ ።

የሚያደራጀዉ ቢገኝ በአምባገነነዊዉ ሥርዓት የተንገፈገፈ ለትግል ዝግጁ ሆኖ የሚጠብቅ የነቃ ሕዝብ አለን ። እዚህም እዚያም የሚፈነዱ የማይታረቁ ቅራኔ ያጫሯቸዉ የሕዝባዊ ቁጣ ነበልባሎች በመታየት ላይ ናቸዉ ። ቋያ ሰደድ ሆነዉ ወያኔአዊዉን የሥልጣን ካብ ወደ አመድነት ይለዉጡት ዘንድ ከፍተኛ ትግልና ያንኑ ያህል መሥዋዕት ይጠበቃል ። የሕዝባችንና የሀገራችን የፍዳ ዘመን እንዲያበቃ ያለዉ የዘረኞች አገዛዝ መገርሰስ ፤ በቦታዉም በሕዝብ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት መገንባት ይኖርበታል ። ለዚህ ደግሞ ያለን ፍቱን ምርጫ አንድ ነዉ ፤ የተባበረ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል /
በነጻነቷ ኮርታ ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

## ደብዳቤዎች

**ደስ ብሎኛል**

ይድረስ ለኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች ፤ ጋዜጣችሁን ሁልግዜም ቢሆን ሳላነባት የቀረሁበት ጊዜ የለም:: ከዚህም በተጨማሪ የፍኖተ ሬዲዮናችሁንም በጉጉት እከታተላለሁ:: የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በመከታተል በምታቀርቡት መረጃ የሚስተካከላችሁ አለ ለማለት ያስቸግረኛል:: ስለሆነም ለናንተ ያለኝ አድናቆት ሁልጊዜም ከልብ የመነጨ ነው:: አሁን ደግሞ ፍኖተ ራዲዮ ወደሳተላይት ተቀይራ በመላው ኢትዮጵያ ልትሰራጨ መሆኗን ስሰማ በእውነት ነው የምለው የተሰማኘ የደስታ ስሜት ከዚህ እስከዚህ ነው አይባልም:: ምክንያቱም ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ማናገር የምትችሉት እናንተ መሆናችሁን አምናለሁና ነው:: ስለዚህ የደስታ ስሜት ፈንቅሎኝ ነው መሰለኝ ከዚህ ቀጥሎ ያለችውን ግጥም ቋጥሬ ለመላክ በቅቻለሁ ፤ በጋዜጣችሁ ላይ እንደምታወጧትም ተስፋ አደርጋለሁ::

ቸር ይግጠመን

ጎርጎርዮስ ከሰሜን አሜሪካ

**ፍኖተሬዲዮ**

አንደበቷ ታንቆ ፣ ላለፉት አመታት፣
በወያኔ ባንዳው ፣ በባዕዳኑ ሀብት፣
ተሰውራ ነበር ፣ ከኢትዮጵያ ርቃ፣
እውነት ስለሆነች ፣ የሀገር ጠበቃ::
<<ግንባርከን አሳየው>> ፣ ዛሬ ግን አበቃ...!
እልል በል ወገኔ ፣ ተነስ ተነቃቃ፤
በጎንደር በጎጃም ፣ በትግራይ አድርጋ፣
በሐረር በባሌ ፣ ጋምቤላ ወለጋ፣
በሳተላይት ሆና ልትገባ ነው አሉ፤
ፍኖተ ሬዲዮ ፣ በኢትዮጵያ ሁሉ፤
ባየር ተምዘግዝጋ ፣ ልትደርስ ፣ ለትግሉ::

ውድ ጎርጎርዮስ
የላኩልን ጽሁፍ ደርሶናል እናመሰግናለን። ገጥምዎንም በዚህ እትማችን አውጥተነዋል።

ፍኖተ ዲሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽን በሳተላይት የማሰራጨቱ ዜና እኛንም አስደስቶናል።

ይህንን የተቀደሰ ዓላማ ለማሳካት በዋሽንግተን ዲሲ ና አካባቢዉ የምንገኝ ደጋፊዎች የገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻ እያደረግን ነዉ።

እርሶም ሆኑ ሌሎች ተባባሪዎቻችን በ ኤፕሪል 18, 2015 ሲልቨር ስፐሪንግ በሚገኘዉ በአቢሲኒያ ሬስቶራንት ውስጥ በአዘጋጀነዉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ እራት ግብዣ ላይ እንዲገኙ ጋብዘንዎታል ።

ከኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

# ዜና ከተባለ

**መሰተዋት ከድሬ**

የሌባ ዓይነ ደረቅ የሰው ልብ ያደርቃል
ወያኔም ካልዋሸ በዚያው ሞቶ ያድራል።

ወያኔ በሀሰት መንደርደሪያ ላይ ተመስርቶ (የብሔር ቅራኔ ዋና ነውና ትግራይ ትገንጠል በሚል)፤ ቅኝ ተገዛሁ የሚል አባት አፍርቶ፡፤ ዋሽቶ ቀጥፎ ለድል የበቃ ቡድን ነውና ካልዋሸም እውነትም ይሞታል ማለቱ አግባብ አለው ።

ወደ ጉዳያችን--ዜናችን-- ስንገባ ደግሞ በስፖርት እንጀምርና የወጣት ቡድን የተባለው ከውድድር ውጪ ተደርጎ ተስፋ አድርገው የነበሩትን አሳፍሯል ። ቁም ነገሩ ግን ይህ ሳይሆን ለብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ተብሎ በወር 18ሺ ዶላር የሚከፈለውም የፖርቱጋል ተወላጅ አሰልጣኝ ብቁ የሀገር ቤት አሰልጣኞች ባሉበት የወጣቶቹ አሰልጣኝ ተደርጎ የስፖርት ፌዴሬሽኑ ገንዘብ በሙስና ሲባክን መክረሙን ለማወቅ ተችሏል ።

ሙስና ካልንማ ዘንድ በወያኔ ስርዓት ሙስና መረን ለቆ በቢሊዮን ደረጃ ብር ወደ ባዕድ ሀገር መጓዙ ሊረጋገጥ ተችሏል። የእነ አዜብ፤ጀኔራል ክንፈ፤ሳሞራ፤ በረከት፤ ስዩም መስፍን ወዘተ ካሸሹት ገንዘብ ባሻገር ዝቅ ባለ ደረጃ ያሉትም ወያኔዎች ከኒው ዮርክ ባንኮች እስከ ስዊስ፤ ባሃማስና ማሌዚያ ባንኮች ድረስ ገንዘብ አስቀማጭ ሊሆኑ ችለዋል ። ዝርፊያው ደርቷል። ለወያኔ ጥብቅና የቆሙ ባዕዳን ራሳቸው አደገ በለጸገ የሚሉት ኤኮኖሚ ህቁን ሊደብቅ አለመቻሉን ማመን ተገደዋል ። በራሳቸው ድምዳሜ መሰረት በኢትዮጵያ ድህነት ካለፈው ብሶና ከፍቶ እንደሚገኝ ግልጽ ሆኗል። ወያኔ ዕድገት የሚለው ለራሱና ለጭፍሮቹ እንጂ ሕዝብን የማይመለከት መሆኑ ግልጽ ሆኗል ማለት ነው ። ወያኔ ዴሞክራሲ ዋና ጉዳይ አይደለም፤ ዋናው ጭንቀታችን ሕዝብን መመገብ፤መጠለያ ማቅረብ፤ ኑሮውን ማሻሻል ነው ብሎ ይመጻደቃል ። ይህ ዕድገት በዴሞክራሲ ፈንታ ብሎ ሊሰየም የሚጥረው ወያኔያዊ ማጭበርበሪያ ግን ባዶ ወይም ከንቱ ወይም ውድቅ መሆኑን የወያኔ አገዛዝና ውጤቱ ያሳያሉ ። የተገኘ ዕድገት የለም--ለወያኔና ጭፍሮቹ ብቻ ካልሆነ። ሚሊዮኖች እንደተራቡ ናቸው ። የኑሮ ውድነት ገደብ አጥቶ ዜጎች ሁሉ በችግር እየማቀቁ ናቸው ። የስራ አጦች ቁጥር በሚሊዮኖች ሲሆን ወያኔ በጥቅሉ ቦዘኔዎች ብሎ ማውገዙን መርጧል ። መንገድ አዳሪው (የጎዳና ተዳዳሪ ይሉታል ሲያደናግሩ--የምን ትድድር! ) ቁጥሩ ወደ ሚሊዮን ሊጠጋ እየዳዳ ነው ። የሀገራችን መሬት እየተቸበቸበ ነው--በቅርቡ ደግሞ የደቡብ--የአዋሳ አካባቢ--መሬት ለሽያጭ እየቀረበ ነው ።

ከዚሁ በተያየዘ ዜና ደግሞ ወያኔ ቀውጢ ቀን ከመጣ በሚል ያቺ ይመኛት የነበረውን ነጻ ትግራይ (ከተቻለ ደግሞ ትግራይ ትግሪኚን) እውን ለማድረግ ሴራውና እንቅስቃሴው ቀጥሏል ። የወያኔ ጎራ ቀቢጸ ተስፋን ማስተናገድ ተገዷል ። አንቀጽ 39ን ሊጠቀምባት አቆብቁቧል ፡፡ የጎንደርና ወሎን መሬት አሁንም በስፋት ወደ ትግራይ እያጠቃለለ ትግራን ሰፊ ግዛት ሊሰጥ እየጣረ ነው ። የመሳሪያና ጥይት ክምችት በትግራይ ማብቂያ ያጣ ሆኗል ። ትግራይ ከፖርት ሱዳን ወደብ ጋር የምትገናኝበትና በአጠቃላይም ከሱዳን ጋር የምትተሳሰርበት ሁሉ መንገድ እየተዘጋጀና እየተጠረገ ነው ። የትግራይ ትግሪኙም ሁኔታ ብዙም ተስፋ ሰጪ ሆኖ አልተገኘምና ወያኔዎቹ ዋና ትኩረታቸው ነጻ ትግራይን እውን ማድረግ ላይ ሆኖ ይገኛል። ይህን እቅድ ደግሞ ውጤታማ ለማድረግ ኢትዮጵያን ማበጣበጥና በማያባራ የእርስ በእርስ ጦርነት መዳረግ ያስፈልጋልና ወያኔ ይህን ፤ለማድረግ ደፋ ቀና እያለ ነው ። የሚደግፉት ባዕዳን ራሳቸው በወያኔ የአሁኑ አያያዝ ከተቀጠለ እንደ ሶማሊያ ኢትዮጵያም የወዳቂ/ውድቅ መንግስት መሆን አደጋ አለ ብለዋል ። ይህን በመቃወም ደግሞ ጸረ ወያኔ ነን እያሉ ግን የትግራይን የበላይነት ደጋፊ የሆኑ ትግራዊ ምሁራን ባለፈው ሰሞን ኡ ኡ ሲሉ ተደምጠዋል ። የትግራይ ምሁሮች ሕዝብን እንጂ ወያኔን መታደግ እንደማይገባቸው ማወቅ ሲገባቸው ዓመታት አልፈዋል ።

ወያኔ 40 ዓመት ሆነኝ ብሎ ሲጨፍር ሲያደነቁረን ቆይቷል ። ሀፍረተ ቢስነቱንም ራሱንና አረመኔ መሪዎቹን በማዳነቅ የለፈፈውና የጻፈው ሁሉ አጋልጦታል። ለወያኔ ዋሾዎች የለመደባቸው መገናኛ ብዙሃን መድረክ ሰጥተው ያው በፈረደበት ኢሕአፓ ላይ እነ ስብሓት፤ አባይ ወዘተ እንዲጨፍሩና ሀሰት እንዲነዙ ረድተዋል ። ተወያኔ መሰል አምባገነን አገዛዞችም ከሱዳን እስከ ርዋንዳ ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኔስቴር ሳይቀሩ ወደ መቀሌ ተጉዘው ሀይ ሀይ ተባብለዋል ። የፈረደበት የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብየው ደግሞ ራሱን አዋርዶ ሲወድቅ መታዘብ ተገደናል ። የካቲት 11 ግን በዓል ሳይሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ የመከራ መጀመሪያ ቀን ነው ። ወያኔ በሻዕቢያ ተረግዤ በደደቢት ተውለድኩበት ያለበት ቀን ነው ! የኢትዮጵያ ጠላት የውልደት ቀን ! የሙሶሊኒ የውልደት ቀን ልናከብር ይጠበቃል ወይስ ግራዚያኒ ሕዝባችንን የፈጀበትን የካቲት 12 የወያኔን ምስረታ ቀን ሆነ ስልጣን የያዘበትን ቀን በዓል ብለው የሚያከብሩ ሁሉ ሀገርን የካዱ ብቻ ናቸው ።

## አስቲ የሚከተሉትን ትኩረት ሰጥተን እናጢናቸው፤

### <u>በአዋሳ ዩኒቨርስቲ በተነሳ ተቃውሞ በርካታ ተማሪዎች ተጎዱ!</u>

በዩኒቨርስቲው ግቢ ለበረካታ ቀናት ለመጠጥም ሆነ ለመጸዳጃ የሚሆን ውሃ በመጥፋቱ የተነሳ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች ከመሸተታቸውም በላይ ተማሪዎቹ ለበሽታ በመጋለጣቸው የተነሳ ተማሪዎቹ ትምህርታችውን በማቆም ለዩኒቨርስቲው አስተዳደር ጥያቄችውን ቢያቅረቡም የዩኒቨርስቲው አስተዳደር የጥበቃ ፖሊሶች ተማሪዎችን በመደብደብ በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን ከአዋሳ የደረሰን ዜና ያስረዳል። በአሁኑ ወቅት በአዋሳ ከተማ በተለይም ከከፍተኛ የትምህርት ተቃማት የሚመረቁ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በሥራ እጦት የተነሳ ለመንገድ አዳሪነትና ለልመና ተጋልጠው ይገኛሉ። ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ ሰሞኑን በጥቁር ውሀ፤ በሻመና፤ በስንቅሌ፤ በወንዶ ጢቃና አካባቢው የሚገኙ ለም የሆኑ የእርሻ ቦታዎችን ለውጪ ቱጃሮች በመቸብቸብ ላይ ሲሆን በአካባቢው ላይ የሰፈሩ በርካታ አርሶ-አደሮችና አርብቶ አደሮች ከማሳቸው ላይ እየተፈናቀሉ መሆኑም ታውቋል።

### <u>ቅርስ ማውደሙ ዘመቻ</u>

በኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ሆቴል ሆኑ ገዳሞች ላይ እየደረሰ ያለው የቃጠሎ አደጋ አነጋጋሪ ሆኖ በአብላጫው ያለው ድምዳሜ የወያኔ ድርጊት ነው የሚል መሆኑ ተዘግቧል ። ይህ የቃጠሎ አደጋ በቅርቡ ዙቋላንም ጎብኝቷል ። ወያኔ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ ነው የሚባለው በሁለት ምክንያት ነው ። 1ኛ/ ወያኔ ኢትዮጵያን ቅርስና ታሪክ አልባ ማድረግ ተልዕኮው ነው፡ 2ኛ/ ወያኔ ቅርሶችን ቀደም ብሎ እየዘረፈ ቃጠሎን ሽፋን ማድረግ ምርጫው ሆኗል።

### <u>የአባይ ጸሃዬ አያባራ ቅጥፈት</u>

40 ዓመትሞላንን አስታከው የወያኔ መሪዎች የከፈቱት ሰፊ የታሪክ ክለሳ ዘመቻ በተለይ ኢሕአፓን በተመለከተ ቅጥፈትንና ጥላቻን ያዘለ ነበር። ምነዋ ይህ ሁሉ ጩኸት የለም ከስሚል በምትሉት ድርጅት ላይ ለሚለው መልስ አልሰጡም ።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ምን ይሰማ……አገር?



**“የኤርትራዉ መሪ ( ኢሳያስ አፈወርቅ መሆኑ ነዉ ) ወደ ኢትዮጵያ የሚሰራጭ የሳትላይት ቴሌቪዥን ማቋቋሚያ ገንዘብ በሚሰጥበት ሁኔታ ላይ በኢያሱ አለማየሁ ከሚመራዉ ኢሕአፓ ጋር ስምምነት አደረገ ።”**

*(ኢትዮ ፓኖራማ የተሰኘ ድረ- ገጽ ዜና ብሎ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያስነበበዉ ፤ ጃንዋሪ ፳፬ ቀን ፪፻፲፰)*

- **ለነገሩ ዉሸት አበዛችሁበት እንጂ ፤ አንዲት ጫፍ ሳትይዙ በባዶዉ አላጎራችሁም ፡፡ ይኼ ኢያሱ የሚባል ሰዉ ስንት ነፍስ ስንት አካል አለዉ ጃል ? ባለፈዉ ዓመት ከድርጅትም ከኃላፊነትም አግዳችሁት ነበር ። ባለፈዉ ወር አዲስ አበባ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ተገኝቶ ያሳተመዉን መጽሐፍ አስመረቀ አላችሁን ። ከአሥር ዓመታት በፊት ደግሞ አሥመራ ዉስጥ ታይቷል ብላችሁን ነበር ። በዚህ አያያዙ የዛሬ ወር ደግሞ ሞቃዲሾ መግባቱ አይቀርምና ያን ጊዜ ደዉሉልን ።**

//

**“በተፈጥሮዬም ሆነ ባለኝ ተሞክሮ ከሳሽ ወቃሽ አይደለሁም ። በዚህ ላይ አሁን ያለሁበት ዕድሜ ከሳሽ ወቃሽ ኖሬ እንኳ ብሆን ለዚያ የሚያመች ዕድሜ አይመስለኝም።…ጊዜ ቆሞ አይጠብቅም / ---ለንስሀ ሞት አብቃኝ የኃይማኖተኛ ጸሎት ብቻ አይመስለኝም”**

(የአሰፋ ጫቦ ግልጽ ደብዳቤ ቅንጫቢ፤ ኢትዮ ሚድያ ድረ ገጽ እንዳሰፈረዉ ፤)

- ***አይጥ መንኩሳ አመሏን አትረሳ” ሆነና በስተማታህ የጀግኖች መቃብር ትጎደፍራለህ ። ከንቱ ተገላባጭ ሆነህ እንጂ ገና ደንደሮ ሳለህ ያልሆነልህን አሁን አንድ እግርህ ጉድጓድ ከገባ በኋላ ይሳካል ብለህ ነዉ ?***

//

**“ የኤርትራ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሀያ አራት ዓመት በኋላ ከኢትዮጵያ ተለየች ።”**

( *ሪፖርተር ጋዜጣ ጃንዋሪ ፳፭ ቀን ፪፻፲፭ የዘገበበት ዜና* )

- ***ይገርማል ፤ ዕቅዳችሁ እስከዛሬ ድረስ መቶ በመቶ አልተጠናቀቀም ነበር ማለት ነዉ ። አሁንስ ምን ያህል ቀራችሁ ?***

//

**“(አንድነት) ለኢአዴግ አመራሮችም ቢሆን ያን ያህል የከፋ አመለካከት አልነበረዉም ። እንዲያዉም እነሱ ሳይጠየቁ የሚያልፉበትን መንገድ ለማመቻቸት ፍላጎት ነበረው ።.....ሰጥቶ ለመቀበል የተዘጋጀ አመራርና ፓርቲ ነበር ።”**

*(አቶ አሥራት አብርሃም የአንድነት ፓርቲ ተ/የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ፍትህ ጋዜጣ ላደረገለት ቃለ መጠይቅ የሰጠዉ መልስ (ኢትዮ ሚዲያ ድረገጽ እንዳስነበበዉ፤)*

- **ለመሆኑ ለወያኔ ምን ሰጥታችሁ ምን ልትቀበሉ ነበር ዝግጅታችሁ ? “ወያኔዎች ሳይጠየቁ የሚያልፉበትን መንገድ ለማመቻቸት” ነዉ ያላችሁት?/ .....እንዲህ ነዉ እንጂ ትግል/**

ከገጽ 3 የዞረ

በወያኔ ቁጥጥር ስር ያሉት መገናኛ ብዙሃን ካቀረቡት ባሻገር በተለይ በአውስትራሊያ ሀገር ያለው የአማርኛ ድምጽ ራዲዮ ማለትም የደርግ ደህንነት መስሪያ ቤት አባል በነበረው በካሳሁን ሰቦቃ የሚተለላፈውና ጸረ ሕዝቦችን ከአረመኔው መንግስቱ ጀምሮ ሲያቀርብ የቆየው ራዲዮ አባይ ጸሓዬን ጋብዞ ሲያስለፈልብን ተደምጧል ። አባይም የመቅጠፊያ መድረክ ስላገኘ ልክ ኢሕአፓ ሲመሰረትም በዚያው ወያኔ እንደተመሰረተ አድርጎ ለማቅረብና ተጨማሪም ውሸት ሊያሻሽጥ ሲጥር ተደምጧል ። ቃለ መጠይቅ አቅራቢዋም የክልሉ ሴት መሆኗ ሊታወቅ ተችሏል ። ወያኔ ወያኔ ቅጥረኞችን ነጻ ራዲዮና ድረ ገጽ ነን በሚሉት ውስጥ ማሰማራቱ ደግሞ ምስጢር አይደለም ።

## ጽንፈኛው በስርቆት ተከሰሰ

አማራን ማረድ መጨፍጨፍ ነው ባዩ ወራዳው ጃዋር ከኦሮሞዎች የመገናኛ ተቋም ከ 280 ሺ ዶላር ያላነሰ ገንዘብ ከነሚስቱ ሆኖ መስረቁን የተቋሙ፡ፕሬዚዳንት አጋለጠው ። ይህ የአሜሪካ የስለላ ተቁማ ቅጥረኛ ነው ተብሎ ሲከሰስ የነበር ግለሰብን መድረክ በቅድሚያ ሰጥተው የነበሩት ጸረ ወያኔ ነን የሚሉት የራዲዮና ቴሌቪዥን ተቋሞች ለግምት የገበቡበት ሲሆን ጽንፈኛው ግለሰብ--እንደ ሁሉ አክራሪዎች--በሆድ ሲመጣበት ቹብረክ ብሎ ተራ ሌባነቱን አረጋግጧል ።

## ልዮ ልዮ


ውሸት የማይታክተው ወያኔ ባዕዳን የሚያጅቡትን የኤኮኖሚ ዕድገት መለፈፉን ቢቀጥልም፤ የዋጋ ማሻቀብ ቀንሷል ብሎ ቢቀጥፍም ተጨባጭና ሀቀኛ አሃዞች በተለይ የምግብ ዋጋ መናሩን አረጋግጠዋል ። የኑሮ ውድነትም ቢሆን በስምንት በመቶ ደረጃ--ወያኔ እንደሚለው--ሳይሆን ቢያንስ ወደ 14 በመቶ አካባቢ ነው ሲሉ ውስጥ አዋቂዎች ያጋልጣሉ ። አሃዝ ለውሸት አመቺ ነው ። ሀቁ ግን የሕዝብን የቀን ተቀን ኑሮ በማየት የሚወሰን ይሆናል ። ሕዝቡ ለረሃብ ተዳርጓል፤ በተለምዶ አነጋጋር ሌላው ቀርቶ ሽሮና ጎመን አሮበታል። የጉርሻ ኤኮኖሚ ነው ያለው--የደርግን የወጀድ ምርት ጥሪ የሚመስል ። ውሸቱን በመቀጠል ለመከላከያ የምናወጣው በጣም ጥቂት ሆኖ ከአፍሪካ ትልቅና ግዙፍ የሚባል ጦር መስርተናል ማለቱን ተያይዞታል ። ወያኔ ለወታደር/ለጦሩ የሚያወጣው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ ሌላ ዜጎችን ወደ ሶማሊያ ወስዶ ስለሚያስጨርስ፤ የሀገራችን መሬት ላይ አሜሪካ የጦር ሰፈር እንዲመሰርት በመፍቀድ ወዘተ የሚያገኘው ድጎማን ክፍያ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላሮች የሚገመት ነው ። ወያኔ ለስለላ መዋቅሩና በትግራይ ለሚያከማቸውም ጦር የሚያወጣው ገንዘብ ኢትዮጵያን እያደማ መሆኑም ምስጢር አይደለም ። ዋና የገንዘብ ወጪ ተቆጣጣሪ (ኦዲት ጄኔራል) የነበረው ለማ አርጋው ወያኔ የሀገር ገንዘብ እያባከነር መሆኑና በተለይም የሚሊቴሪ/የጦር ተቋሙ ዋና ተጠያቂ መሆኑን በማጋለጡ ወይም በማቅረቡ ከስራ ቦታው እንዲለቅ ተደርጎ የወያኔ ባለሟል የሆነው ገመቹ ዳቢሶ ተክቶታል ።

ወያኔ ታላቋን ትግራይ እውን ለማድረግና ካስፈለገም ገንጥሎ የትግራይ ትግሪኚ ግቡን ለማሟላት በሚል ከጎንደር መሬት ዝርፊያውን የቀጠለ ሲሆን ይህን በተመለከተ የተነሳውን አመጽም ለማጥቃት ባለው አቅም ሁሉ እየተሯሯጠ መሆኑ ታውቋል ። የጠገዴና የወልቃይት እንዲሁም የአርማጨሆ አርሶ አደሮች ላይ የአፈና እርምጃ መውሰዱን ቀጥሎበታል ። በትጥቅ ትግል ተሰማርተናል የሚል ክፍሎች ይህን የሕዝብ ቁጣና አመጽ በተጨባጭ ለመርዳት እስካሁን ያደረጉት ምንም ጥረት የለምም ተብሏል ። ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ በእቅድና በውሳኔ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋን ማዳከም በሚለው ስምሪቱ ቀጥሎ የአማርኛ ቃላትን በባእድ ቋንቋ እየተካ መሆኑን ታዛቢዎች ገልጸዋል ። የአማርኛ ቃላትና ስያሜዎች ላሏቸው ሁሉ እንግሊዝኛን እየተካ እንዳለም ሁሉም እየታዘበው ያለው ነው ። ሌላ የመገናኛ ቋንቋ ይኑር የሚል በተለይ ኦሮሚፋን አስመልክቶ የሚቀርበው ሀሳብ እንዳለ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ግን የዚህ ጉዳይ አቀራረብ ከጀርባው ወያኔያዊ ተንኮል አለበት ሲሉ ብዙዎች ጠቁመዋል ። በአዲስ አበባ የህዝብ ቁጥር ስለበዛና በቂ ንጹህ ውህም የማግኘት እድልዋ የመነመነ በመሆኑ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ወደ ሌላ ቦታ ይቀየር በሚል ወያኔዎች ውይይት ጀምረዋል የተባለውም--በምስጢር ቢያዝም-- አይሆንም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም እየተባለ ነው ።

በርከት ያሉ መሰል ዜናዎች አልጠፉም ። የሀገራችን ሰው እንደሚለው ግን ወሬ ቢበዛ በአህያ አይጫንም። የወያኔን ገበናና ወንጀል እናውቀዋለን ። የቀረን ግዳጅ ወያኔን መጣል ነው ። ታጥቀናል መጣንበት የሚሉትና ጠመንጃ ወድረው ዝናር ተሸክመው የሚታዩትን ብንጠብቅ ብንጠብቅ የመድረክ ፋኖዎች ከመሆን አላለፉም ። መሳቂያም እየሆኑ ነውና ሀገራችንን ከውድቀት ለማዳን ለመራራው ሁለገብ ትግል እንነሳ። መስዋዕትነት ጠያቂ መሆኑን ሳንዘነጋ።

ቸር ይግጠመን !

Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC. 20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላልን። ለቀለም ፣ለሹርባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ሰራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon




ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-4217 |
| ኢሜል፡ | espic@aol.com |
| ፖስታ፡ | EPRP<br>P.O. Box 73337<br>Washington, DC. 20056 |
| ድረ ገጽ፡ | eprp.com |

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-5832 |
| ኢሜል፡ | eprpylnew@gmail.com |
| ፖስታ፡ | EPRPYL<br>5309 Georgia ave.<br>Washington, DC. 20011 |
| ድረ ገጽ፡ | eprpyl.com |

# ትናንትና

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተከሉ ከራሞት

### ፪

ራሴን ለመደበቅ የተጠቀምኩበት ሽፋንም ፈጽሞዉኑ ተራ ነበር ። ሳደርገዉ የነበረዉ ቀለማማ ዐይነርግብ ከፊቴ ገጽ ላይ የራሱን አሻራ አሳርፎ ነበርና ለጸሀይ ተጋልጦ ይበልጥ ከጠቆረዉ የቆዳዬ ቀለምጋር ሲወዳደር ያለዉ ልዩነት በቀላሉ ይታያል ። ደበከበከ ብሎ ከወደ መቀመጫዬ ጠብሰቅ የሚል ሰዉነት ፤ እንዲሁም ቀይና ትንሽ ልጅ የሚያስመስል ፊት ነበረኝ ። የምለብሰዉ ጥለት የሌለዉ ተራ የሸማ ቀሚስ ቢሆንም አሳማኝ አለባበስ እንዳልነበረ ይታወቀኛል ። ጎረቤቶቻችንም ቢሆኑ ሲያናግሩኝ የማይባቸዉ ሁኔታም ሆነ የሚያሳዩኝ ፊት ፈጽሞ ቢጤያቸዉ አድርገዉ እንዳልተቀበሉኝ ያሳብቅባቸዉ ነበር ።

ከህቡዕ ቆይታዬ የመጀመርያዎቹን ሦስት ቀናት በባልና ሚስቱ አስጠጊዎቼ አልጋ ላይ የአልጋልብስ ተከናንቤ አሳለፍኩ ። ማስመሰያ ምክንያቴ ያዉ ከወለጋ እስከ አዲሳባ ያደረግኩት ረዥም ጉዞ ያደረሰብኝ የአካል ዝለት ነበር ። በአራተኛዉ ቀን ግን የድርጅታዊ ግንኙነቴን መስመር መልሼ ከዘረጋሁ በኋላ ወደ ደጅ ወጣሁ ። ፍጹም ግራ ከመጋባቴም በላይ የሁሉም ሰዉ ዐይን የሚመለከተኝ መስሎ ተሰማኝ ። በስጋት ተዉጬ በአራቱም ማዕዘናት ዙርያዬን አማትር ጀመር ። በርግጥም የሚከተሉኝ ጥቂት ዐይኖች አልታጡም ። እነዚያ ዐይኖች ግና የማንም ሳይሆኑ መናኛ ዕድል ሞካሪ- የቅንዝረኛ ሽማግሌዎች ዐይኖች ነበሩ ። ከወሎ ጠቅላይ ግዛት መምጣቴን የገመተ አንድ ሽማግሌ ፤ ራሱም የወሎ ሰዉ መሆኑን ከነገረኝ በኋላ በወርቅና በጌጣጌጥ ስጦታ ሊያባብለኝ ሙከራ አደረገ ። ከዚያም አልፎ ሊቆነጥጠኝ ሲሞክር ባለ በሌለ አቅሜ ስገፈትረዉ ያዩ ሰዎች ሳቁበት ፤ ተሳለቁበትም ። ይህን መሰሉን የወንዶች ጸባይና ድርጊት ብዙም ሳልቆይ የተላመድኩት ሲሆን በገሃዱ ህይወት ዉስጥ የሀገሬ ሴቶች የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ለማገናዘብ በቅቻለሁ። በራስ መተማመኔ እየሄደ በመጣ ጊዜም እኔዉ ራሴ ከቅንዝራሞቹና ከቢጤዎቻቸዉ ጋር ሆን ብዬ መላከፉን ገፋሁበት ። አልፎ አልፎ ጥሩ ሽፋን ሆኖ አገልግሎኛል ። በጨካኝ ወንድ ክህደት ሳቢያ ከተማ ዉስጥ ብቻዋን የምትሰቃየዉን ሴትና በመሰል ትርክቶች ዉስጥ የየዋሂቱን ግልገል ባህሪ ተላብሼ መጫወቱን ተካንኩበት ። ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ዙርያ የሚያጠነጥን ወሬ ደግሞ በአዉቶቡስ ተራና በተመሳሳይ ሥፍራዎች ተመድበዉ የሚሰማሩትን የደኅንነት ሠራተኞች ጆሮ ለመሳብ የሚበቃ ጣዕም እንደማይኖረዉ ግልጽ ነበር ።

በጥቅሉ ሲታይ ፤ ምንም እንኳ አንዳንዴ ስቃይ ባያጣዉም ፤ ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ራሴን ያዛመድኩበት የሽግግር ጊዜ ፈጥኖ ሊያልፍ ችሏል ። እንደቀድሞዬ በመኪና ሳይሆን፤ አዘዉትሬ በእግሬ መጓዝ ነበረብኝና ወፍራሞቹ ጭኖቼ ከሚያደርጉት የርስ በርስ ፍትጊያ የተነሳ የቆዳ ሽፍታ ወጣብኝ ። በንፍፊቶቼ ዕባጭ ህመም በጣም ተሰቃየሁ ። የሰዉነቴ ክብደት በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ዉስጥ በብዙ ቀነሰ ።ይሁን እንጂ አቋራጭ መንገዶችን ና መሿለኪያዎችን ከማካለል አልተገታሁም። የአዲስ አበባን ትርኪምርኪ መኖሪያ ሠፈሮች ፤ በጫጫታ የተሞሉትን የመሸታ ቤቶቿን ፤ የሻይ ቤቶቿንና የገበያ ሥፍራዎቿን አበጥሬ አወቅኳቸዉ ። ትምህርት ገበየሁ ። የምኖርባትን ከተማ ጠረን ፤ ሠዋራዎቹን ሥፍራዎቿን ፤ ጠመዝማዛ ጎዳናዎቿንና አቋራጭ መንገዶቿን ፤ በአጠቃላይም የዉሎ አዳሯን ምትና ድምጸት ለማወቅ በቃሁ ።

እያደር ፤ ራሴን ከሚተራመሰዉ የሰዉ አጀብ ተለይቼ የማልታወቅ - እንዲያዉም ፈጽሞ በዐይን ልታይ የማልችል አድርጌ ቆጠርኩት ። የቀድሞዉን መሥርያ ቤቴንና እኖርበት የነበረዉን አፓርተማ አልፌ በእግሬ እስከመጓዝ ደረስኩ ። በእያንዳንዱ ቀን ማለዳ በእግረኞቹ መተላለፊያ ላይ ፤ ከባህላዊዉ ሸማ ቀሚሶቻቸዉ ላይ የመሥሪያ ቤታቸዉን ስምና ዓርማ የተጠለፉባቸዉን ካፖርቶች የደረቡ ሠራተኞች የተቀየጡባቸዉ ሴቶች እጅብ ብለዉ እየተንጫጩ እምብዛም ገቢ ወደማያስገኝላቸዉ ሥራ ሲያመሩ መመልከት የተለመደ ነዉ ። ወደተለያዩ የቀጠሮ ሥፍራዎች ሳመራ አዘዉትሬ ራሴን ከነርሱ ጋር እቀይጥ ነበር ። አልፎ አልፎ ቢሮዬን ከሚያጸዱልኝ ሴቶች ኋላ ሆኜ በሄድኩባቸዉ አጋጣሚዎችም አንዳቸዉም እንኳ አላወቁኝም ።

ከነርሱም ሆነ ከዚያ ቀደም ከሚያዉቁኝ ሌሎች ሰዎች ጋር ፊትለፊት ሳልገጣጠም የቀረሁበት ጊዜ ሳይኖር ቀርቶ አልነበረም ። ሆኖም አንዳንዴ ዐይን ራሱ ከሚያየዉ ይልቅ ያላየዉን አምኖ የሚቀበልበት ጊዜ አለ ። ጓዶቼ እኔ ስለምገኝበት ሥፍራ ሆን ብለዉ ግራ የሚያጋቡ ወሬዎችን አሰራጭተዉ ነበርና ያዩኝ ሰዎች ዐይኖቻቸዉን ማመን አልቻሉም ። እርግጥ ነዉ ፤ ይህ አይነቱ ዘዴ ለተወሰነ ጊዜ ሠርቷል ።
ፈጽሞ ልላመደዉ ያልቻልኩት አንድ ነገር ቢኖር ገበያ ዉስጥ በዋጋ ተከራክሮ መገበያየቱን ነበር ። ይህ ሁኔታዬ በተቀሩት ሴቶች ( በቸርቻሪዎቹ ባለጉሊቶች ዘንድ ሳይቀር ) በጥርጣሬ እንድታይ ቢያደርገኝም ድርጊቴን ማስደገፊያ አዘዉትሬ በምላሽ የማቀርባቸዉ ጮርቃ ምክንያቶች ጥርጣሬዉን በማለዘብ ዐመኔታ ያስገኙልኝ ይመስላል ። በዚህ መልኩ የገዛኋቸዉን አትክልቶች የሞላሁበትን ቅርጫት አንግቤ ወዳሻኝ ሥፍራ መንቀሳቀስ ችያለሁ።

ከአትክልቶቹ ሥር ወይም አንዳንዴ በቅርጫቱ ዉስጥ ተያይዞ በተሠራ ልዩ መደበቂያ ዉስጥ በስዉር የሚበተኑ ወረቀቶች ፤ ወይም የተፈታታ ጠመንጃ ፤ ሽጉጦች ፤ፖስተሮች ፤የማባዣ ቀለሞች ፤ ጥይቶች ወይም በህቡዕ ለሚደረገዉ ትግል አስፈላጊ የሆነ ማናቸዉም ቁሳቁስ በስዉር ይጓጓዛል ። ቅርጫቱን በማልጠቀምበት ጊዜ የመቢያ ሳህኖችን ወይም የሚያብረቀርቁ ሽክላ ሰር የወተት ማለቢያዎችን የምገለገል ሲሆን በድብቅ የማጓጉዛቸዉን ነገሮች ከሥር በማድረግ ከላዩ እንጀራ አስቀምጥበታለሁ ። አንዳንዴም ከቋንቋ ዉጭ የተመሰጠሩ ( የኮድ) መልዕክቶች በዉስጣቸዉ የተጎሰጎሱባቸዉን ዳቦዎች ተሸክሜ እንቀሳቀስ ነበር ። የተለያዩ ቁሳቁሶችን የምናጓጉዝባቸዉ በርካታ ዘዴዎች ነበሩን ። በዚህ መልኩ በተለያዩ ሽፋኖች በመንቀሳቀስ የአገዛዙን አዉታሮች ከዕይታ ዉጭ ሆኖ የሚያመሰቃቅለዉ የህቡዕ ሠራዊት አካል ከሆኑት (ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ከተዉጣጡት በብዙ መቶዎች ከሚቆጠሩት ) ሴቶችና ወጣት ልጃገረዶች ጋር አብሬ ተሰልፌአለሁ ።

በአንደኛዉ ወር ቆይታዬ ፤ ህቡዕ በሆነዉ ህይወት ከጨቅላ ህጻንነት ተነስቼ ወደ ጉልምስና ልመነደግ በቃሁ ። በመጠለያነት ስገለገልበት የቆየሁበት ቤትም ከጊዜ ወደጊዜ የማያመቸኝ እየሆነ ሄደ ። በተለይም ጓዶቻችን በ፩፱፻፷፰ ዓ.ም መጋመሻ ላይ ( እ.ኤ. አ ፌብሯሪ 8 ፤1976 )መርካቶ ከሚገኝ አንድ የመንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ብር ለድርጅታችን ጥቅም እንዲዉል ካደረጉ በኋላ ፤ የፖለቲካ ብስለት ያልነበረዉ የቤቱ ደባል ለጥቅም የማጎብደድ ሃሳብ በአዕምሮዉ የሚመላለስ መሆኑ ይታይ ጀመር ። በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዉስጥ ተቀጥሮ የሚሠራበትን የጥበቃ ሥራ እንዳያጣ በመስጋቱ "ርጉማኑን ሥርዓተ አልበኞች" መላልሶ ማዉገዝ አመጣ ። ሌላዉ ችግር የተጠለልኩበት ቤት ክፍሉ እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ ለመጻፍም ሆነ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሕትመት ሥራ የማያስችለኝ ነበር ። ተበታኝ ወረቀቶችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለመደበቅም አስቸጋሪ ሆኖ አገኘሁት ። በተጨማሪም በድርጅታዊ ሥራ ከምገናኛቸዉ ሰዎች ጥቂቶቹ ወደቤት መምጣት መጀመራቸዉ ለጥርጣሬና ለቀበሌዎች ዐይን የሚያጋልጥ በመሆኑ የተነሳ ሌላ ቤት መቀየር የግድ ሆነብኝ።

አድራሻ ቀይሬ የገባሁበት አዲሱ ቤት ደግሞ እንደኔዉ ተደብቀዉ የሚኖሩ ሌሎች ሰዎችን ያዳበለ ነዉ ። ምንም እንኳ ስለማንነታችንም ሆነ ስለተሰማራንበት ተግባር ርስበርስ ገልጠን ያላወራን ቢሆንም ፤ ወዲያዉኑ የነርሱዉ ቢጤ መሆኔን ለመገመት አልተቸገሩም ። በዚህም ሳቢያ ይህኛዉንም ለቅቆ መሄድ ነበረብኝ ። ይህኛዉን ቤት ትቼ ከወጣሁ ከሦስት ቀናት በኋላ መጠጊያ ባደረግኩት አዲስ አካባቢ መኖር ጀመርኩ ።

በዚያ ከቶ በማይዘነጋ ቀን ድፍን አዲስ አበባ በተባራሪ ወሬ ይንቻቻ ነበር ። ያን ዘግናኝ ዕለት ፈጽሞ አልረሳዉም ። የሠራተኞች ማህበር( ኢሠማኮ ) ና የኢትዮጵያ ሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ግንባር ቀደም ታጋይ የነበረችዉ ዳሮ ነጋሽ ፤አራት ኪሎ በሚገኘዉ የመኖሪያና የሥራ ቦታዋ በሆነዉ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አጠገብ በግፍ ተገደለች ። ግድያዉን እጅግ ዘግናኝ ፤ የገዳዮቿን ወንጀልም እጅጉን የከፋ የጭካኔ ድርጊት የሚያደርገዉ ዳሮ በተገደለችበት ወቅት ወሯ የገባ ነፍሰ ጡር የነበረች መሆኑ ብቻ አልነበረም ። ገዳዮቿ ሆዷን ቀድደዉ ሽሉን የዘረገፉት ሲሆን አንድ የዐይን እማኝ እንደገለጸዉ ከሆዷ ያወጡት ህጻን ለተወሰነ ጊዜ ነፍሱ አልወጣችም ነበር ። ይህንን የሰማዉ ሕዝብ እጅጉን ተደናገጠ ። የግድያዉ ዜና እንደ ሰደድ እሳት ተዳረሰ ። የዜናዉን ተዐማኒነት የተጠራጠሩ ወገኖች የተወራዉ ዉነት መሆኑን በገዛ ዐይኖቻቸዉ አይተዉ ለማረጋገጥ ወደ ግድያዉ ሥፍራ ጎረፉ።

በዚያን ቀን የተካሄደዉ ግድያ የዳሮ ብቻ አልነበረም ። ቅድስት ማርያም ካቴድራል አጠገብ አንድ መነኩሴ ፤ የድሮዉ አዉሮፕላን ማረፊያ አጠገብ ሦስት ሠራተኞች ፤ ሰበታ አካባቢ አምስት ሰዎች ፤ በተለያዩ አካባቢዎችም በርካታ ዜጎች ተገድለዋል ። አገዛዙ ያሰማራቸዉ ነፍሰ ገዳዮች ያሻቸዉን አድርገዉ አምሮታቸዉን በመወጣት ተጠምደዉ የዋሉበት ልዩ ቀናቸዉ ነበር ። በዚያኑ ዕለት ግንፍሌ ድልድይ አጠገብ አራት መምሕራን መገደላቸዉንና ሬሳቸውም በአንድ በመስኖ በለማ አነስተኛ የአታክልት ሥፍራ እንደተጣለ ሰማሁ ። በፍርሀት እየተንዘፈዘፍኩ ወደተባለዉ ሥፍራ በጥድፊያ አመራሁ ። ከተገደሉት መሃከል አንደኛዉ የመጀመሪያ መጠለያዬ የነበረዉ ቤት ባለቤት የሆነዉ መምሕር መሆኑን ተረዳሁ ። የፊቱን ገጽታ አይቶ መለየቱ በፍጹም አዳጋች ነበር ። ሆኖም በለበሰዉ ፤ ሽክላማ ቀለም በነበረዉና የሚስቱ የእጅ ሥራ በሆነዉ ሹራብ ለየሁት ።

እነዚህን መሰል ፖለቲካዊ ግድያዎች የሕዝቡን የቁጣ ጩኸት ቀሰቀሱ ።ገዳዮቹ ደግሞ በነዋሪዉ ዘንድ የማይታወቁ አልነበሩም ። ነፍሰ ገዳዮቹ ታጣቂዎች በጉራ የተወጠሩ ጀብደኞች፤ ያለአንዳች ማንገራገርና የኅሊና ወቀሳ የፈለጉትን ሰዉ ተኩሰዉ የሚገድሉ ናቸዉ ። ቀዉሱ ግርማ ከበደና በርሱ የሚመሩት ነፍሰ በላዎች አራት ኪሎ አካባቢ በዳሮ ነጋሽና በሌሎቹም ላይ ለተፈጸመዉ ግድያ በቀጥታ ተጠያቂ ናቸዉ ። በሰዉ ስቃይ የሚደሰቱት እነዚህ አረመኔዎች ፤ ገደብ ባልነበረዉ ግብረ ሽብራቸዉ ወታደራዊዉን መስተዳድር ለከፋ ትችት አጋለጡት ። በዚህም ሳቢያ በስተፍጻሜዉ ፤ ለጥፋት አስታጥቆ ባሰማራቸዉ አገዛዝ አላዉቃችሁም ሊባሉ በቅተዋል ።

ይቀጥላል........

★ዴሞክራሲያ★
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 5 የካቲት 2007 ዓ.ም.

## የካቲት ሲታወስ---የሕዝብ ድል አይቀሬ ነው

የካቲት ለኢትዮጵያዊን ሁሉ ልዩ ሥፍራ ያላት ታሪካዊ ወር ናት። የካቲት በአንድ በኩል በነፃነትና በአገር ፍቅር ስሜት ልባቸው እየነደደ መስዋእት ሆነው ያለፉትን ወገኖቻችንን በቁጭት ሲያስታውሰን በሌላ በኩል ደግሞ በእነሱ መስዋእትነት ውጤት በሆነው ድል አንገታቸንን አቅንተን በመሄዳችን በቃልም ሆነ በፅሁፍ ሊገለፅ የማይችል ስሜት በአእምሮአችን ውስጥ ይጭራል።

የነፃነት ግንብ ፈራርሶ በወደቀበት ያ የጨለማ ዘመን ነፃነታችንን አንነጠቅም ፤ ክብራችንን አናስደፍርም በማለት በርካታ ኢትዮጵያዊያን መስዋእት ሆነዋል። በትግላቸውም የአገራቸውን አፈር በደማቸው አቡክተው የባርነትን አለት በአጥንታችው ጠርበው የነፃነትን ግንብ አንጸውበታል።

"አንድ ሕዝብ ታሪኩን ሲያስታውስ በቅርሱ ለመኩራራት ወይም በጎደለው ለመሳቀቅ ሳይሆን ካለፈው ጠቃሚን ትምህርት ለመቅሰምና ይህንንም ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ነው። ተስፋን ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፍ ዜጋ ሁሌም ሕያው ነው። ታሪክን የማስታወስና የመዘክር ልምድ የሕዝብ ጸጋ ነው። በየካቲት 66 የፈነዳው ሕዝባዊ አብዮት ግፈኛን ሥርዓት ከማስወገዱ ሌላ የሕዝብን የትግል መንፈስና ጽናት፣ኀብረት፤ ቆራጥነት በሚገባ አሳይቷል። ከሰላሳ ዓመት በፊት። ግፍ የለመደች መሬት ሆነችና ሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዝብ ድል በአምባገነኖች ተነጠቀ ። የያኔው የ17 አመቱ እንክርዳድ በተራው ጊዜውን ጠብቆ ሲታጨድ ደግሞ ሌላ እንክርዳድ፤ ራሱን ወያኔ ብሎ የሰየመ አረም ፈልቶና ሀገርን ጨምድዶ ይዞ እነሆ በየካቲት 66 በደም ታጅበው ተስተጋብተው የነበሩ የህዝብ ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ አልባ ሆነው የሕዝብን ስቃይ ገላጭ ሆነው በመቀጠል ላይ ናቸው ።" (ዲምክራሲያ--ግፍ አይፈሬ መሬት እንክርዳድ ያበቅላል)

ቀድሞም ቢሆን በዘር በሃይማኖት፤ በፆታና በፅድሜ ሳይከፋፈል እንደ አንድ ሰው በመሆን የጠላትን ወረራ ለማክሸፍ “ ከዘላለም ባርነት ያንድ ቀን ነፃነት፤ ባንዳ ተለይ ” በሚል መፈክር ዙሪያ ተሰባስቦ፤ በአርበኝነት ተሰማርቶ ለአገሩ ነፃነት የሚፈለገውን መስዋዕትነት ከፍሏል። በዚህ ጦርነት የፋሽስት ጦር ባደረገው ኢ-ሰብአዊ ጭፍጨፋ በርካታ ህፃናት፤ ሴቶችና አረጋዊያን ሰለባ ሆነዋል። የዚህ አይነቱ ጭፍጨፋ በዓለም ታይቶ የማይታወቅ መሆኑ ቢነገርለትም የኢትዮጵያን አርበኞች የዓላማ ፅናት አላናጋውም። እንዲያውም ለነፃነታችው ሲሉ በወደቁ ጀግኖች ምትክ ለአገራችው ሉዓላዊነትና ለባንዲራችው ክብር ሲሉ በወደቁ አርበኞች ምትክ ቁጥር ሥፍር የሌላችው ወጣት የነፃነት ታጋዮችን ማፍራት ቻለ እንጂ ከጀመረው ትግል አላዘናጋውም። የካቲት 12 የዚህ መስዋዕትነትና ጀግንነት መታሰቢያ ቀን ነው ። ይኸው በአይነቱ የመጀመሪያው የሆነው የኢትዮጵያዊያን የየካቲት ገድል ማንንቱ ተረስቶና ተረግጦ በቅኝ ግዛት ቀንበር ሥር በሚማቅቅበት ወቅት የተገኘ ድል በመሆኑ የኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ሕዝብ ድል በመሆኑ አገራችንን የአፍሪካዊያን የነፃነት ተምሳሌት ሲያሰኛት ይኖራል።

የካቲት የድላችን አርማ ነው፤ የካቲት ለአገራችው ሲሉ በግፍ የተጨፈጨፉ ኢትዮጵያዊያን ሰማዕታት መታሰቢያ ነው። የካቲት ጠላት በጎሳና በሃይማኖት ከፋፍሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደም በማቃባት ሥሩን ሊሰድ ያሰበበትና የከሸፈበት ወር ነው። በተለይም አሁንም ሆነ መጪው ትወልድ እስከዛሬና ለመጪውም በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በምሬት የሚታሰበው የካቲት የፋሽስት ጭፍጨፋ የነዚያን ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችንን የአገር ፍቅር ስሜት ዘወትር እንድናስበው ያደርገናል። የአገራችውን ክብር በጠላት ከርስ መቃብር ላይ ለማረጋገጥ በዛሬው የአዲሳባ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ በግራዚያኒ ላይ ቦምብ በመወርወር የአገርና የወገንን ፍቅር ሰሜት የገለፁት አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ይታወሱናል።

የጀግኖች አባቶችንና እናቶችን የአርበኝነት ፈለግ በመከተል መሬት ለአራሹ ይሁን፤ዳቦ ለተራበው ይሰጥ፤የሃይማኖትና የፆታ እኩልነት ይከበር የሚለውን መሠረታዊ የትግል መፈክር ያስተጋቡት ምሁሮች ብዙሐኑ አርሶ አደር ሕዝብ ከብዝበዛ ተላቆ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን ሲጠይቁ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በገሀድ ይታይ የነበረውን የብሔረሰብ ጭቆና ደግሞ በዝመታ ሊያልፉት አልቻሉም። የኢትዮጵያን አንድነት በጭቆና ላይ መሥርቶ ለማረጋገጥ መጣር የማይሠራና ኢሰባዊ ነው ያሉት እነዚህ ምሁራን ለሀገራችው ደህንነትና አንድነት ውድ ህይወታቸውን ለመስጠት የተነሱ፤ በኋላም የሰጡ በመሆናችው የሕዝብ አንድነት በዴሞክራሲና በሕዝብ መብት መረጋገጥ ተመሥርቶ ለሀገር አንድነት መገንቢያ ይሁን ሲሉ ተሟግተዋል።

የየካቲተ 1966ቱ የለውጥ እንቀሰቃሴ (አብዮት) ጥሪ “ድብብቆሽ ጠፍቶ ሐቁ ተገልጦ ይውጣ ” ጭቆና አለና እናስውግደው ፤ተባብረን እንነሳ ፤እኩልነትን እናረጋግጥ፤ ሀገራቸን ከኋቀርነት ተላቃ እንደሌሎች የበለጸጉ አገሮች በእደገትና በልማት ጎዳና ትጓዝ በሚል ቆራጥ መንፈስ የተደረገ እንጂ የአፍ አርበኞች እንደሚሉት በጎጠኞችና በባዕዳን የተጠነሰሰ ሴራ አልነበረም።

ከላይ ያሰፈርነው ሐቅ የዚያን ትውልድ ራእይ የሚያመላክት ብሩህ ተስፋን ለሀገሩ ከሰነቀ ትውልድ የታለመ በጎ ህልም ነበር። ዛሬም ነው። በመሆኑም ሕዝባዊነቱ ሊካድ የማይችለው የየካቲቱ እንቅስቃሴ፤ ላባደሮች፤ ተማሪዎች፤ አብዮታዊ ምሁራን፤ መምህራን፤ የመንግሥትና የቢሮ ሠራተኞች፤ ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎች፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፤አርሶአደሮች የተሳተፉበት እንቅስቃሴ ነበር። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በወቅቱ ከፍተኛ እልቂት እያደረሰና በአፄው መንግሥት ተደብቆ የነበረውን ድርቅና ረሃብ ይፋ በማውጣትና የባለሥልጣኖቹንም እኩይ ተግባር በማጋለጥ ትልቅ ሚናን ተጫውተዋል። መምህራንና ተማሪዎች "ሴክተር ሪቪው" በመባል ይታወቅ የነበረውን አዲስ የትምህርት ፖሊሲም አጥብቀው በመቃወማቸው ለየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የማይናቅ አስተዋፃኦ አበርክተዋል። የዚያ ትውልድ የተማረው ክፍል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል አምርሮና አጠንክሮ መጠየቅና መመርመር የጀምረ፤ የሀገሩን የሩቅና የቅርብ ሁኔታዎችን በመገምገም በአገራቸን ይታይ የነበረውን ኋላቀር ሥርዓትና በዓለም ደረጃም የቅኝ ግዛትን መሰፋፋት በመቃወም ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ የተሻለ ሥርዓት የሚመሰረትበትን በጎ ራእይ ያነገበ ተራማጅ ትውልድ ነበር።

የካቲትን ስንዘክር በሀገራችን ውስጥ ትምህርትን፤ ሕክምናን ፤ሥራን ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ የብዙሃኑን መብትና ጥቅም በእኩልነት ለማስከበር፤ የብሔር ጭቆናን ለማስወገድ ፤በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነትን ለማሰረጽ ፤ማኅበራዊ ፍትህን ለማስገኘት ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ እድገትን ለማምጣት ትልቅ ዓላማን አንግቦና ብሩህ ተስፋን ይዞ የተሰባሰበ፤ ከራሱ ጥቅም ይልቅ ሀገሩንና ሕዝቡን ያስቀደመ ለመሠረታዊ ለውጥ የቆመ ትውልድን የምንዘክርበት ታሪካዊ ወር ጭምር ነው የካቲት።

" (ያ ትውልድ) ለሕዝብ እታገላለሁ ብሎ ስለተነሳ ስርዓቱ ሲያባብለው ግን አልከዳም፤ አልተገዛም ቃሉን አለወጠም፤ ቃል ኪዳኑን አላፈረሰም ። ሆዱን ወዶ፤ አፉ ክዶ፤ ክፉ ለምዶ አለነበረም ያ ትውልድ ። ትግል ቆራጥነትን ይጠይቃልና አስፈላጊውም ወኔ ነበረው። ትግል መስዋዕትነትን ይጠይቃልና ለሀገሩና ለወገኑ ሊሰዋ ዝግጁ ነበር--ተሰውቷልም ። የካቲት 66 የዚህ ቆራጥነትና ሀገር ፍቅር መንፈስ ነጸብራቅ የሆነው ትግል ውጤት ነው። የናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደተባለው ደግሞ ኅብረተሰብ አንድ ወጥ አይደለምና፤ ቅራኔዎች የለውጥ አዋላጅ ናቸውና፤ በየመደቡ በየፈርጁ ለጥቅሙ መቆም የሚጠበቅ ነውና የሕዝቡ ድል በታጠቀው ክፍል ሲነጠቅ ለባለነፍጥ ያደሩ ጥቂቶች አልነበሩም። ደርጉ የሕዝብን ድል የነጠቀ ኃይል ሳይሆን መብትን አስከባሪና ለውጥን አረጋጋጭ ነው ያሉ አብረውት ተሰልፈው ለራሳቸውም ለሕዝብም መከራ የሆነን አገዛዝ ደገፉ፤አጠናከሩ። ሥርዓቱ የግፍ አገዛዙን ለመጠበቅ በባዕዳን ተደግፎ የሽብር ክንዱን በሕዝብ ላይ ሲያሳርፍም የተከተለውን አሰቃቂ እልቂትና ፍጅት ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። በዚያ ክፉ ዘመን ደግሞ ራዕዩን ያልረሳውና ወኔውን ለጭብጦ ያልቀየረው ክፍል ታሪክ ዘወትር በሚዘክረው ጀግንነት አረመኔውን መንግስት ታግለ መስዋዕት ሆነ። ዛሬ ይህ ዓይነቱ ቆራጥነትና ለሀርና ዓላማ ታማኝነት አጥቶ አንዳንዴም ጸረ ወያኔው ከመለስ ደጋፊው አልለይ እያለ ባስቸገረበት ወደ ኋላ መለስ ብለን የየካቲቱን 66 ተመክሮ መገምገም ማስታወሱ ጠቃሚ ይሆናል"። (ዴሞክራሲያ)

የአፄው አገዛዝ ለተለዋዋጩ የአገራችን የፓለቲካና ማኅበራዊ እውነታ ተገቢውን መልስ ለመስጠት አለመሞከሩ ሕዝብን ያሳተፈ ዴሞክራሲ እንዲመጣ ለተደረገው ትግል ለቀረበው ለሕዝብ ጥያቄ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ማለቱ ለብሔር ብሔረሰብ እኩልነትን አለማረጋገጡ ፤ የመሬት ሥርዓት ለማሻሻል አለመፈለጉ የሃይማኖት እኩልነትን አለማረጋገጡ ትውልድን ጎጂ የሆነ የትምህርት ሥርዓት በመቅረፁ ወዘተ... የተነሳ የመደብ ቅራኔው በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲያድግና እንዲከር በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተበታተኑ የሸፍትነት ባህሪ ያላቸው በዝቅተኛም ደረጃ ቢሆን የድርጅት ቅርፅን የያዙ የአመፅ እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉና ሕዝቡ ለትግል እንዲነሳሳ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ውድቀቱንም ጋብዟል ማለትም ይቻላል ። በወቅቱ በተለይም በሀገራችን ደቡባዊ፤ ሰሜናዊና፤ምሥራቃዊ ክፍሎች ተበደልን ተረገጥን የሚሉ ብሔር/ብሔረሰቦች በትጥቅ የተደገፈ እንቅስቃሴ በማድረግ ከኃይለሥላሴ አገዛዝ ጠባቂዎች ጋር መጋጨታቸው ሥርዓቱ በቅራኔዎች የተሞላ መሆኑን አረጋጠዋል። በመጨረሻም የአፄው አገዛዝ በአገሪቱ የተከሰቱትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በሠላምና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ባለመቻሉ በጠብ-መንጃ ሃይል ለታጠቀ ወታደራዊ አገዛዝ አገሪቱን አሳልፎ በመስጠት ራሱም ጠፋ።

የአፄውን አገዛዝ የተካው ወታደራዊ የምርጥ መኮንኖች(የደርግ) አገዛዝ ሥልጣን ይዞ በቆየበት አሥራ ሰባት(17) አመታት ለአገዛዙ አስጊና ተቀናቃኝ ወይም የተለየ ሀሳብ ያላቸውን ንጹሃን ዜጎች በተለየም የተማሪውንና ለዚያች አገር ከብርና እድገት ይንገበገብና ይቆጭ የነበረውን ታጋይ ትውልድ በመፍጀት በመላው አገሪቱ የሰቆቃና የእልቂት መዓትን አወረደ። የአገሪቱንም ኢኮኖሚ ወደአዘቅት እንዲወርድ በማድረግ ሕዝቡ ለረሀብና ለከፋ ድኸነት እንዲጋለጥ አደረገ። የደርግና የአጋሮቹ ወንጀል ዛሬ ጊዜ አልፏል በሚል የሚረሱም ወይም የሚበረዙም ሊሆኑ አይችሉም። ፈርጣጩ ኮልኔል ኢትዮጵያን አሽመድምዶ ለወያኔ ሰጣት፤ ኢትዮጵያን ካዳት፤ አጠቃት። ደርግን የተካው የወያኔ አገዛዝ በኃይል የሚኒልክን ቤተመንግሥት ከተቆጣጠረ ጀምሮ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጎጥና በጠባብ ብሔርተኝነት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲን በመንደፍ የአንድን ቡደን አምባገነንነት አንግሷል። በአገዛዙ መዋቅሮችና በአያሌ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች፤ በሙያ ማህበራት፤ በሲቪክ ድርጅቶችና በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ጣልቃ በመግባት የዜጎቸን መብት በመደፍጠጥ በማን አለብኝነትና በፈላጭ ቆራጭነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ዘላቂ ጥቅም በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በመጉዳት ኢትዮጵያዊነትን በፅኑ እያዳከመ ይገኛል። አገዛዙ የዴሞክራሲና የሰላም ጠንቅ በመሆን ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች በአገራችው እንዳሻቸው ተደራጅተውና በነፃ ተዘዋውረው፤ የፖለቲካ አመለካከታቸውንና ዓላማቸውን ለሕዝቡ አስረድተው በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዳይሳተፉ አግዷል። የተለየ እመለካከት አላቸው የሚላቸውን ምሁራን ከሥራ አባሩዋል፤ የአገዛዙን የጎጥ ፖሊሲ የተቃወሙትን አገር ወዳድ ዜጎችን በመጨፈጨፍ፤ ፤ በማሰርና በማሳደድ ያሸብራል ። ወያኔ ለባእዳኑ ተንበርክኮ የእነሱን ጥቅም አስጠባቂነቱን ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ጠላትነቱን በሁለንተናዊ መልኩ እያሰመስከረ ይገኛል። ወያኔ የራሱን ሕገ-መንግሥትና የደነገጋቸውን ሕግጋትና ደንቦች ሳይቀር ያለምንም ይሉኝታና ሃፍረት በመጣስ የአንድ ፓርቲ የበላይነትን አንግሷል ፤ በሕዝቡ ዘንድ ፍራቻና ጥላቻን ያሳደረ ፍጹም አምባገነናዊ ቁጥጥርን በመላ አገሪቱ ላይ አስፍኗል።

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 5 የካቲት 2007 ዓ.ም.

በፌዴራሊዝም ሥም አገዛዙ ባለፉት ድፍን ሃያ አራት(24) ዓመታት የገነባው የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነትንና ፍጹም አምባገነንነትን ነው። ሥልጣን ላይ እንደወጡ ሲፎክሩበት የነበረው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የሰብዓዊ መብት መከበር፤ የአገር ሉዓላዊነትን በማስደፈር፤ በአፈናና ግድያ እንዲሁም በሽብር ተተክተው የአገዛዙን ማንነት በአደባባይ አጋልጠውታል። ዛሬ በህወሓት/ወያኔ አባላት ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ያሉ ድርጅቶችና የንግድ ተቋማት በሚደረገላቸው ልዩ የሆነ አድሏዊ እንክብካቤ አብዛኛዎቹ በሚደንቅ ሁኔታ ከመቅጽበት እየበለጸጉ ሌሎቹ ደግሞ እየተዳከሙ፤ እየተገለሉና እየተዘጉ በመሄድ ላይ ይገኛሉ። በአገሪቱ የሚገኙ ልዩ ልዩ የሆኑ የኢኮኖሚና የንዋይ ተቋማት በህወሓት ድርጅት አባላትና ቤተሰቦች እንዲያዙ በመደረጉ ተጠቃሚዎቹ የአንድ ቡደን አባላትና ቤተሰቦች ሲሆኑ፤ የተቀረው ዜጋ የበይ ተመልካች ለመሆን ተገዷል። ከውጪ በብድርና በእርዳታ በሕዝብ ሥም የሚገኘውን ንዋይ በሕገ-ወጥና ዓይን ባወጣ የዘረፋ -አሠራር ከባእዳኑ ጋር በመመሳጠር የግል ኩባንያዎቻቸውን በማጠናከርና ለክፉ ቀን ይሆነናል በማለትም በቢሊዎን የሚቆጠር የሕዝብ ሐብት በአውሮፓ፤ በአሜሪካና በኤሽያ ባንኮች በማከማቸት ላይ ናቸው። የገዥው ፓርቲ በሚከተለው የይስሙላ "የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ" ሥርዓት የሚታየው በንግድና በልማት ሥራ ላይ የተሠማሩትን ታታሪና ብቃት ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን የአገዛዙ አባል ባለመሆናቸው ብቻ የንግድ ፈቃድ፤ብድርና የወጪ ምንዛሪ ላይ በሚያወጣቸው የተዛቡ ሕጎች የተነሳ ማነቆን በመፍጠር በንግዱና በልማቱ እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ በማድረግ ተስፋ አስቆራጭ ደባን ይፈጽማሉ። ስለሆነም ከአገር በቀል ባለሀብቶች ይልቅ የባእዳኑ ቱጃሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። በአጠቃላይ ወያኔ የሚያቀነቅንውና የሚካሂደው የኢኮኖሚ ሥርዓት በባለሙያዎች በቂ ጥናትና ዝግጅት ያልተደረገበትና ፍጹም አቅጣጫውን የሳተ፤ ለአድሎአዊ አሠራርና ለንቅዘት የተመቻቸ በመሆኑ እነሆ የአገራችን ኤኮኖሚ ለከፋ አደጋ ተጋለጦ ይገኛል። በአጠቃላይ የችግራችን ምንጭ የሆነው የወያኔ አገዛዝ እስካለተወገደ ድረስ የአገራችን ሰቆቃና ስቃይ ማባሪያ የሌለው ለመሆኑ መጽሐፍ ገላጭ አያስፈልገውም።

በየካቲት 1966ዓ.ም. (የዛሬ 41 ዓመት) የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ያነሳቸው መሠረታዊ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ዛሬም አልተመለሱም። የዚህ ሕዝባዊ እንቀሰቃሴ ዓቢይ ዓላማ በአገሪቱ ፍትህ የሰፈነበት ሥርዓት መትከል በመሆኑ እሰካሁን በተከታታይ በአገራችን የተተኩት አገዛዞች አምባገነን በመሆናቸው ሕዘባዊ ትግሉ አሁንም በሂደት ላይ ይገኛል። ይህ ትግል ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ማደረግ ሲሆን ታዳሚዎቹም ሕዝብና የሕዘብ ወገኖች ብቻ ናቸው። ሌላ ሕዝብን ለሥልጣን የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ የለም። የሕዝብ ትግል የሚያመጣው ለወጥ ሥር- ነቀልና ጠንካራ የሀገር መሠረት የሚጥል በመሆኑ የሀገርና የሕዝብ ጠላቶች ይጠሉታል ፤ይፈሩታል፤ በጽኑም ይታገሉታል። የሕዝባዊ ትግል ግቡ እሩቅ መንገዱም ዳገታማና ጠመዝማዛ፤ ጉዞውም አድካሚ ነው የሚባለውም ይህንን ሁሉ ፈተናና መሰናክል ማለፍ ስላለበት ነው።

"የየካቲት 66ን አብዮትና የሕዝብን ታሪካዊ ትግል..ስንዘክርም አንዱን የካቲት ሸኝቶ ሌላውን ሲቀበል የከረመው የሀገራችን ሕዝብ ዕጣው ከጅብ ጎሬ ወደ ጅብ ዋሻ ቢመስልም በትግሉና በመስዋዕትነቱ ታሪክን መቃኘቱ፤ ማደሪያውን- ዕጣውን ሊለውጥ ሊያሻሽል መዋደቁን ለመመዝገብ ነው ። የገገርዎች ዜና መዋዕል መሠረትነቱ ተሰርዞ፤ አንጀቱን በድግ ጠፍሮ-አስሮ ከተፈጥሮም ከባለሥልጣኑም ተጋትሮ ይህቺን ሀገር በላቡና በደሙ ማንነቷን የለገሳት፤ አሻራውን አሳርፎባት ሀገር ያደረጋት ብዙኃኑ ጭቁን ሕዝብ ትንሽ ምላጭ ሀገር ትላጭ እንዲባል በተናቀው ክንዱ የጀመረው ጉሸማ--ትግል የሥርዓትን ለውጥ ወልዷል። በየካቲት 66 ሕዝባዊ ትግል በግንባር ቀደምትነት ከተሜው ጎልቶ ቢታይም ሥርዓቱ የሕዝብን እንቃስቃሴ እንዳያኮላሽ እንቅፋት የሆነበት የትግሉ መፈክሮች፤ ዋነኛ ጥያቄዎች የሕዝብን መሠረታዊ ብሶትንና ፍላጎቱን ያስተጋቡ መሆናቸው ነው። የወቅቱ ታጋይ ምሁራንም ሚናቸውን ሲፈርጁ በሕዝብ አንደበትነት በመሆኑ መሬት ለአራሹ ብለው ሲፋለሙ፤ እኩልነት ብለው ሲዋደቁ፤ ሠራተኛው ሕዝብ ባለመብት ይሁን ብለው ሲሰለፉ፤ ዕድሉ ለተነፈገው ግና ግሮ ጥሮ ላስተማራቸው ሠፊ ሕዝብ ላንቃ ሆኑት እንጂ፤ መፈክሩን አነገቡለት እንጂ ሌላ ዓላማም ሆነ ግብ አልነበራቸውም። የየካቲት አብዮት ሲገመገም ኋላ የተከሰተው መርገም ግንዛቤን የሚለውጥ መሆን የለበትም። አብዮቱ--በርግጥማ የሥርዓትን ለውጥ ያስከተለ ትግል ነበርና--ከተሳታፊዎቹ የየግል ይዞታና ዕምነት ባሻገር የጭቁኑን ሕዝብ በታሪክ ሠሪነት አለሁ ባይነት ያስመዘገበና ያንን የገለማ-- ግን በዕብሪትና በግፍ የጨቀየውን-- ሥርዓት ያዋከበና የደረመሰም ነበር። የካቲት አብዮት በደርግ ተብዬው ማጅራቱን ቢመታም አዲስ ገዢ መደብ ቤተመንግስት ከመግባቱ በፊት የበሰበሰውን ሥርዓት አስወግዷል። የየካቲት አብዮት ደርግን አልወለደም፤ በዝባዡን የአጼውን ሥርዓት ግን ቀብሯል"። (ዴሞክራሲያ የካቲት 1991 ዓ.ም.)

በዚህ በተራዘመ ሕዝባዊ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለው መስዋእትነት እጅግ የከፋና የመረረ ድሉም እንደዚያ የራቀበት ምክንያት ከላይ በሐቅ የተነሳ ነው። ሕዝብን ለሥልጣን ባለቤትነት የሚያበቃው ግዙፍ ድል መስዋእትነት መጠየቁ መጠርጠር የለበትም። በዚህ መስዋዕትነት የማታ ማታ ድሉ አይቀሬ መሆኑን እርግጠኞች ነን። የማይናወጠው ፅናታችንም ምንጩ ይኸው በሕዝብ ላይ ያለን ፍፁም የሆነ እምነት ነው። የአገርና የሕዝብ ፍቅር ስሜት ጠብቆ ለማስተላለፍ የካቲትን ታሪክ በሚገባ መመርመርና ማወቁ ተገቢ ነው ።የዛን ዘመኑ ትውልድ የመሠረታዊ ለወጥን አስፈላጊነት አምኖ የታገለበት ምክንያት ከላይ በስፋት እንደተጠቀሰው የሚወዳት ሀገሩን የበለፀገች ለማድረግ፤ ለህዝቡም ፍትሓዊ ሥርዓትና ዕድገትን ለማስገኘት፤ የአገርን ህልውናና የዜጎቸን አንድነት የሚፈታተኑ ወቅታዊ ችግሮቸን በቅጡ በማጤን መፍትኄ ለመጠቆምና ለመሻት ይበጃል ብሎ ያመነበትን ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ በማሰብ ጭምር ነው። ዛሬን ያን የታገለ ትውልድ የሚያወግዙ--ብዙዎቹ ከአረመኔው ደርግ አብረው ትግሉን ሊያጠፉ ህዝብን የጨፈጨፉ- ሊሸፍኑት ያልተቻላቸው ሀቅ የትውልዱን ጀግንነት፤ ቆራጥነት፤ ሕዝባዊነትና ሀገር ወዳድነት ነው ። ትውልዱ ለምን ግቦች ተነስቶ እንደተሰዋም ዛሬ መደበቅ ወይም ማጣመም የሚቻል አልሆነም ። በየካቲት 1991 ዴሞክራሲያ ሰፍሮ የነበረው የሚከተለው አሳምሮ ያጠቃልለዋል።

" ጥቅጥቅ ባለው የፊውዳል ደይን ቀቢጸ ተስፋ ሰፍኖ ለውጥን መመኘት ከዕብደትና ቅዠት ይቆጠር በነበረበት በዚያን ጊዜ የሕዝብን ሉዓላዊነትና አቸናፊነት አምነው አትናገሩ ሲባሉ ድሃው ይናገራል ብለው በድፍረት ለፍፈው፤ አትድፈሩ ሲባሉ ደፍረው፤ ለሆዳችሁ እደሩ ተብለው ሲሸነገሉም እምቢኝ ብለውና

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 5 የካቲት 2007 ዓ.ም.

ሥርዓቱም ትምህርቱም--ቁሱም መጽሓፉም--ለባለስልጣን መስገድን ባነገሰበት በዚያን ጊዜ አይቻልምን በይቻላል ተክተው፤ ቃልን ከገቢር አዋህደው፤' የግፉዓን ጠበቃ፤ሓዋርያም ሰማዕትም " ሆነው በትግሉ ግንባር የተሰለፉትን ምሁራንና ታጋዮች ሁሉ የየካቲት ዝክረ ታሪክ በነጻ የተጻፈ ምዕራፍ ይለግሳቸዋል። በጥቅም አለመታለላቸው፤ ማመናቸው፤ መድፈራቸው፤ ገዝፎ የነበረው ሥርዓት፤ ያ በባዕዳን ይደገፍ የነበረው ሥርዓት በ "ድህው " ሕዝብ ትግል ይሸነፋል ብለው በጽኑ ማመናቸውና ዕምነታቸው ላይ ተመሥርተው መታገላቸውን ዛሬ ዛሬን በዛሬነቱ በአንጻርነቱ ስናይ በአድናቆት የምንዘክረው ይሆናል"።

ዛሬም ጸረ ወያኔ የካቲት እውን ሊሆን ይችላል ። ቅድመ ሁኔታዎችን መጠየቁ ግን አይቀሬና መዘንጋትም የሌለበት ነው ። የካቲት 66ን በግብታዊነት የፈነዳ ማለቱ የተለመደ ሆኖ ቢገኝም ማንኛውም የሕዝብ አመጽና አብዮት ግን የሕዝብ ስብጥርጥር ትግሎች ክምችት ውጤት ነው ። ከየካቲት አብዮት ፍንዳታ በፊት የአርሶ አደር አመጾች፤ የላባደሩ ትግሎችና አድማዎች፤ የተማሪዎች ትግል፤ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ወዘተ ብልጭ ድርግም እያሉ ተካሂደዋል ። ይህ ሁሉ ሥርዓቱን ሸርሽሮና አዳክሞት እንደነበር ግልጽ ነው ። በአሁኑ ወቅትም ያሉት የሕዝባዊ ትግል ሙከራዎች ከተጠናከሩና ከተስፋፉ ወያኔ ላይ የሚፈነዳና የሚያስወግደው አመጽ ሊከሰት መቻሉ የሚጠበቅ ነው ። ሌላው አስፈላጊውና ወሳኙ ሁኔታ ደግሞ ትግሉ የተባበረና ኢትዮጵያዊ ይዘት ያለው መሆኑ ነው ። በየካቲት 66 ወያኔና መሰል ገንጣዮች የበላይነት አልነበራቸውም፤ የሚደመጡም አልነበሩም ። በወያኔ ከፋፋይና ዘረኛ አገዛዝ 24 ዓመት ካሳለፍን በኋላ ግን ሁኔታው መቀየሩ አልቀረምና እንደ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለማመጽ ያሉት ጋሬጣዎች በቀላሉ መታየት የሌለባቸው ናቸው ። በየካቲት 66 ምንም እንኳን የተወሰኑ ምሁሮች በጥቅም ታውረው ትግሉን ከድተው ብዙ ጉዳት ቢያደርሱም በወቅቱ ግን አብዛኛው የተባባረና በጋራም ሥርዓቱን የጠላና ሊያፈርስ የተነሳ ነበርና ድልን በዚህ መስክ ሊያገኝ ችሏል ። ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ተሟልቶ አይገኝም --ጠንካራ ተቃዋሚዎች የሉም ገና። ይህን ድክመት ማስወገድ ከተቻለ የካቲት 66 እንዳስተማረው አይበገሬ የመሰለው ሁሉ ከአውሎ ነፋስ እንደተጠጋ ዱቄት ይተናል ። ከዚህም ተይይዞ ሌላ ሊሟላ የሚገባው መስዋዕትነትን ይመለከታል ። በትግሉ ብዙ ዜጎች ስለተሰዉ፤ ደርግን ወግድ ባለው ትግል አያሌ መስዋዕትነት በመከፈሉ ሕዝብ ተፈጀ፤ ያታገለው ድርጅት ወጣቱን አስፈጀ ብለው የሚለፍፉ ፈልተዋልና የካቲት የሚጠይቀው ድፍረት በቦታው አልገኝ ብሎ አለ ። ሰላማዊ ትግል የሚባለውም በጠነከረ መንገድ የሚካሄድ ሳይሆን ለእጅ መስጠትና ጀምሮ ላለመቀጠል ማጠየቂያ ሆኗል ። ስለዚህም ለጸረ ወያኔ የካቲት ለመሰዋት ዝግጁ ሆኖ መገኘትን የግድ የሚል ይሆናል ። የሕዝቡን ትግል የሚያደናቅፉትንና የሚከፋፍሉትንም ማሸነፍ ያስፈልጋል ። የጠራና የቆረጠ የሕዝብ ጎራ እውን ከሆነ የካቲት 66 በወያኔ ላይ ይበልጥ አምርሮ፤ ይበልጥ ተጠናክሮ ሊመጣበትና ሊደረምሰውም ይችላል ። ይህንንም በተመለከተ የካቲት 91 በወጣው ዴሞክራሲያ መደመደሚያ ይህን ቅጽ እንዘጋለን።

" ..ደርግ ሲወድቅም ሽግግሩ ሕዝብና ሀገርን በጠቀመ መንገድ እንዳይከናወን ወያኔና ባዕዳን እንቅፋት ሆኑ። ሕዝብ በመስዋዕትነቱ ያስገኘውን ድል ልክ እንደ የካቲት ተቀምቶ፤ መብቱን ተነጥቆ፤ የሀገሩ ይዘት ሳይቀር ሲቀየር በተመልካችነት ተገዶ ተመደበ ። ይህም ጸረ ሕዝብ አገዛዝ በአፍ ደረጃ የካቲትን ማጅራት ከመታው ኃይል የተለየ መስሎ ቢቀርብም በአምባገነንነቱ ተመሳሳይ ሆኖ የፈጸመው ሁሉ እነሆ ዛሬ ዞሮ ለራሱም ለሀገራችንም መዘዙ በዝቷል ። ሄደ ስንለው እየተመለሰ፤ ሞተ ስንለው እያንሰራራ የጭቆናና ብዝበዛ ሥርዓት ዛሬም በላያችን ተሰይሟል። መሬት ለአራሹ ዛሬም ወቅታዉ መፈክር ነው። ዴሞክራሲ ለብዙኋኑ--ዛሬም ወቅታዊ ነው ። መብት ለጭቁኑ-- አሁንም መፈክራችን ነው። ላባደሩ አይበዝበዝ፤ ሠራተኛ ባርያ አይደለም ስንል የነበረው ዛሬም መጮህ ያለበት ነው። የብሐረሰቦች እኩልነት-- ዘረኛ ሥርዓት ዓይኑን በጨው አጥቦ ተሰይሟልና ይህም መፈክር ወቅታዊ ነው ። የሀገር ሉዓላዊነት--ከመቸውም ጊዜ በበለጠ የትግላችን ዕምብርት

ሆኖ ይገኛል ። የየካቲት ዋና ዋና መፈክሮች ዛሬም ሕያው ናቸው። በትግል ያገኘናቸው ድሎች የማይካዱ ቢሆኑም የታገልንላቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ዛሬም ትግልን ምላሽን ይጠይቃሉ ። ከመቸውም ጊዜ የከፋው ሁኔታ ደግሞ ከሥልጣን ጥሜት ሌላ ሀገርን ማጥፋት ተልዕኮው የሆነ ቡድን ለቤተ መንግሥት መብቃቱ ነው። ሀገርን መጠበቅና ከጥፋት ማዳን ወሳኝ በሆነበት ወቅት ላይ ደርሰናል። ለዚህም ነው የካቲትን በጥሞና ዘክረን ከታሪክ ተምረን፤ የነበሩ ጉድለቶችን አስወግደንና በስፋትና በጽናት ተባብረን በጋራ ጠላት መረባረብ የሚጠበቅብን ። የካቲትን በትግል መዘከራችን ተገቢ ነው። የካቲት ማለት ትግል፤ ቆራጥነትና ሀገር ፍቅር ማለት ነበር፤ ነውም። ኢሕአፓ ታሪኩ ከየካቲት አብዮት ጋር የተቆራኘ እንደመሆኑ መጠን ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን በማክበር በየካቲት የአመጽ መንፈስ ዛሬም ጸንቶ ለሀገርና ለሕዝብ ትግሉን ቀጥሏል። በባሩድ ሳይታጠን፤ በተፋፋመ ትግል ሳይታጀብ በሰላምና በዕልልታ የካቲት አብዮት የሚዘከርበት የሕዝብ ጊዜ፤ሕዝባዊ ሥርዓት እስኪመጣም ይህ ትግሉ ይቀጥላል።" ይህ የዛሬ 16 ዓመት በፊት ከተጻፈ መልዕክት በተጨማሪ ሊባል የሚቻል የለም ።

የካቲት አብዮት በትግል ይዘከራል !!__

## እንጻፍ ካልንማ ——3

ኢያሱ ዓለማየሁ

እንጻፍ ግጥም
የአነ ተስፋዬን ተስፋ ያቀፈ
የአምሃን አምሀ የወረሰ
የጸጋዬን ጸጋ የለበሰ
የእነአበራሽን ብርታት የቀመሰ
የእነጋይምን ትዕግስት የታገሰ
እንጻፍ ግጥም የቀላ
በነዳዊት ደም በእነ አብደላ
እንጻፍ ግጥም የሰላ
የጨቋኝ መንጋን የሚቀላ
የነጻነት ክቡር ዜማ
የሙብት የሰብዕና ማወደሻ
እንጻፍ ግጥም መቀስቀሻ
ሰውን ለሰውነት መጋበዣ
የባርነትን እንቅልፍ ማስወገጃ
ቅሌት ውርደትን መሰረዣ
ፍቅር ተስፋን መቀስቀሻ
ክፋት ጥላቻን መጨረሻ።
እንጻፍ ግጥም የተስፋዬን ተስፋ
የጸጋዬን ጸጋ
የሰማዕትን ክብር መላበሻ ።

*ሀማ ቱማ* (1992 ዓ.ም.)

እንጻፍ ካልንማ ሁሌም ሀቅን እንጻፍ።

በቅርቡ ገጣሚው አሊ ሑሴን ውሸት ቪዛ አይጠይቅ ፤ ቲኬትም አይገዛ በሚል ትምህርታዊ ግጥም አቅርቧል። ውሸት ግን ይበራል፤ ይከንፋል፤ ይጦዛል፤ ሀቅን ያጠቃል፤ ዳገትን ሆነ ህግና ፖሊሲን አይፈራ ሀገርን ያጠፋል። በሀሰት ላይ በተመሰረተ ታሪክ ነኝ በሚል ድምዳሜ ላይ ቆመው ቅዠትን እውን ሊያደርጉ የሚባዝኑ ብዙዎች መኖራቸውን የሀገራችን ታሪክ ያሳየውና እያሳየም ያለው ነው። ኢትዮጵያ ታሪኳ የመቶ ዓመት ብቻ ነው፤ አሊያም ሀገር የሆነችው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ ነው ያሉን አወቅን ባዮች ባያምኑትም እያሰራጩ ይህንንም እንደ ገደል ማሚቴ የሚያስተጋቡላቸው ባዕዳንም አግኝተዋል። በኢሕአፓ ላይ እየተሰራጩ ያሉት የሃሰት ክሶች ውሸት ሀፍረት የለው የሚያሰኙ ናቸው። ሀቅ ጊዜ ጠብቆ ያቸንፋል ተብሏልና የጊዮርጊስን የበላ ይለፈልፋል እንዲሉ ዛሬ የድርጅቱን ሀቀኛ አቅዋም መስካሪ የሆኑ ትላንት ይከሱት የነበሩት ናቸው።

በስለላ ዓለም ዘረኛ ብቻ ሳይሆን ሁሉን መጥፎ ነገር ጥቁር የሚሉት ፈረንጆች ጥቁር ፕሮፓጋንዳ የሚሉት አለ። በአጭሩ ሀሰትን በብጣቂ ሀቅ ጠቅልሎና ሸፍኖ እንደ ሀቅ ማቅረብን ይመለከታል። በጥንቃቄ ካልተደረገ ከሽፎ በአሰራጩ ላይ ጉዳትን ያደርሳልና ሙያተኛ አያያዝን ይጠይቃል ። በጠራራ ጸሐይ በሬ ወለደ ማለቱ ያዋርዳልና ጠላት የተባለውን ለመጉዳት የሀሰትን ክስ በስልት ሀቅን አስመስሎ ማቅረብ ያስፈልጋል ማለት ነው ። ወያኔ እንደ አቅሚቲ ባዶ ሰለስተ (ሶስት) የሚለው መሰል ሀሰትን አሰራጭ ክፍል ነበረው ። ሀሰትን ሀቅ ብሎ ለማሳመን ውሸቱ መቶ በመቶ ውሸት ሆኖ መቅረቡ ቀሽም ስራ ነው ። ጎጂና አደናጋሪ ውሸት ብጣሽ ሀቅን ይዞ በዚህ ዙሪያ ሀሰቱን ማጠንጠን መቻል አለበት ። በተለይ የእኛ ዓይነቱ ጠርጣራ ሕዝብ "ማን ያውቃል? ወይ ጉድ" በሚል እንዲያምን፤ እንዲጠራጠር ማለት ነው ። የኢትዮጵያ አድርባዮችና የውሸት ጠራቂዎች ችሎታ እንዳየነው ደካማ በመሆኑ ገና አፋቸውን ሲከፍቱ የሚናገሩት ሁሉ ውሸት መሆኑን አብዛኛው ያውቀዋል ። ግባቸውን አያሟሉም፤ ይከሽፋሉ ማለት ነው ። ጥሬ ስጋ በሊታ ህዝባችንም ‘’ብላ የበሰለ፤ አውራ የመሰለ’’ ማለቱን ብዙዎች የረሱት ይመስላል ። ለሰባቂ ጆሮን አትስጡ በማለት ፈንታ አሳማኝ ውሸትን ቅደዱ ብሎ መምከሩን የከጀልነው ሊሆን አይችልምና መነሻችን ዋሾዎቹ በዚህም ስምሪታቸው መደዴ ናችው ለማለት ነው ። በውሸቱ ሜዳም እርስ በርሳቸው አይስማሙም ።

የኢሕአፓን ምስረታ እንደ ምሳሌ እንውሰድ ። ያበቃለትን ሬሳን ሁሉ ቀስቅሶ ቃልና መድረክ መስጠት የለመደበት አንድ የራዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ ሞት ራሱ ሊወስድ የተጠየፈውን ወንጀለኛ አዛውንት ለመድረክ አቅርቦ በሃቅና በኢሕአፓ ላይ ፏሉል--ጨፍር ብሎ ሲፈቅድለት የለፈፈው ውሸት አለ-- ድርጅቱ በሻዕቢያ ተመሰረተ ብቻ ሳይሆን በሀገራችን የተካሄዱትን የአይሮጵላን ጠለፋዎች የጠነሰሰው ይሀው ሻዕቢያ ነው የሚል። ቀደም ሲልም ሌሎች ቀባጣሪዎች ታሪክ ብለው ሳያፍሩ የጻፉትና የጮሁትም ሊጠቀስ ይችላል። በድርጅቱ ላይ የሚዘምቱት ውሸታቸውን ሊያቀነባብሩ እስካሁን አልቻሉም ።

# ነጻ ሀሳብ

ከደርግ በፊት ጸረ ኢምፔሪያሊስት ሆኖ የቆየውና--አሁንም የሆነው--ድርጅት በኢምፔሪያሊዝም ሊቋቋምና ሊደገፍ የሚችል አልነበረም ። የውሸት ወራሾች ግን ታሪክ ሲሉ ኢሕአፓ የተመሰረተው በምዕራብ ጀርመንና በ አልጄሪያ ነው ሲሉ ደንባራ ምስክርነት ሰጡ ። በዚያን ጊዜ ምዕራብ ጀርመንና አልጄሪያ ሰልፋቸው ተጻራሪ እንደነበር ሰዉ አያውቅም ብለው ነው ማለት ነው ። ሞት ሊወስደው እንኳን የተጠየፈው ወንጀለኛ ሽማግሌና ሌሎችም ደግሞ ኢሕአፓን የመሰረተው ሻዕቢያ ነው ሲሉ ድርጅቱ ሲመሰረት ሻዕቢያ የሚባል ድርጅት እንዳልነበረ እንኳን ማወቅ ተስኗቸዋል ወይም አውቀው ለማወናበድ ተነስተዋል ።

ኢሕአፓን ማን መሰረተው? ድርጅቱ ሲመሰረት ሻዕቢያ አልተመሰረተም ነበርና ይህ ጉድ መሰረተው የሚሉ ነጭ ውሸት እየዋሹ ነው። ወያኔና ሻዕቢያ ድልን ስለተገጎናጸፉ በርካታ ዜጎች በተቸናፊ መንፈስና ቀቢጸ ተስፋ ሁሉን የኢትዮጵያውያን ትግል የኤርትራ ጽንሥ ነው ብለው ለማመን ዝግጁ ሆነዋል ። በራስ ላይ የመተማመኑ ጉዳይ ሰጥሟል። የሽንፈት ምልክት ነው - እጅ የመስጠት። ኢትዮጵያንና ዜጎቹዋን ዋጋ ማስጣት። ኢሕአፓ ሲመሰረት ሻዕቢያ ገና አልተቁቋመም። ጀብሀም ቢሆን ከድርጅቱና መስራቾቹ ጋር የነበረው ግንኙነት ይህ ነው የሚባል አልነበረም። ድርጅቱ የተመሰረተው በኢትዮጵያ ተራማጆች በራሳቸው ነው ። የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴም በሁሉም ተራማጅ ኢትዮጵያውያን የተመሰረተና የተካሄደ ነበር። የካቲትም እንዲሁ የሕዝብ እንቅስቃሴ ነበር እንጂ የትግራይ ትግሬኚ ጠባቦች ክንውን አልነበረም። ወደ ተጨባጭ ዝርዝሩ ስንገባ (የኢሕአፓ ታሪክ ዘርዘር ብሎ በሚያውቁት ሲጻፍ በሰፊው የሚቀርብ ይሆናል) በዚያን ወቅት በተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ጥቃቱ ሲያይል ፤ ከተማሪው እንቅስቃሴ በስተጀርባ የተጀመረው የ መደራጀት ጥረት እየተጠናከረ ሲመጣና በግንዛቤም ቢሆን ትግሉ የደረሰበት ደረጃ መሪ የፖለቲካ ድርጅትን ይጠይቃል የሚለው ሲታመንበት ድርጅት መመስረት ያስፈልጋል የሚለው ድምዳሜ ላይ ተደረሰ ። የድርጅቱ ጥንሥስ በመጀሪያ የሚመለከታቸው ታጋዮች አራት ሲሆኑ ብርሃነ መስቀል ከከርቸሌ ሲለቀቅ የእቅዱ አካል ሆኖ ለቀረበው የአይሮፕላን ጠለፋም ድርጊት ተባባሪ በመሆኑ ሌሎች ቀሪ ሁለት ግለሰቦች ደግሞ በንቃታችው ሳይሆን በሌላ መመዘኛዎች መሰረት እንዲታቀፉ ተደርጎ ሰባት ሆነው ጠለፋው ከባሕር ዳር ወደ ካርቱም በነሐሴ 1961 ተካሄደ ። ሻዕቢያ ያልነበረ ከመሆኑ ሌላ ማንም የውጭ ሀይል ወይ ድርጅት በ ጠለፋው እጅ አልነበረውም ። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ምንም በራሳቸው ማድረግ አይችሉም ብለው ለሻዕቢያም ለባዕዳንም የተጎነበሱ ክፍሎች ሁሉን ነገር የሰራው ሻዕቢያ ነው ወዘተ የሚለው ልፈፋ የዋሾዎችን ዝቅጠት ያሳያል እንጂ ከሀቅ ጋር ግንኙነት የለውም። የኢሕአፓ ምስረታ ሂደትም በዚሁ መልክ የቀጠለ ነው ። እነ መስፍን ሓብቱ፤ ዘሩ ክህሸን፡ ዋለልኝ መኮንን፤ ጸሎተ ሕዝቅያስና ጸጋዬ ደብተራው ሙሉ በሙሉ የተሳተፉበት ጥረት ሆኖ በተጨማሪም ተስፋዬ ደበሳይንም ማቀፍና ማሳተፍ ችሏል ። በቅርቡ አንድ ቀባጣሪ ግለሰብ ተስፋዬን በተመለከተ ሊያሰራጭ የሞከረው ሀሰት አሳፋሪ ሲሆን ተስፋዬ ከጉባኤው በፊት ወደ አዲስ አበባ ተጉዞና በመስራች ጉባኤው አጀንዳ ላይ ከነ ጸጋዬና ደብተራው ጋር ተወያይቶ ውሳኔያቸውን/ሀሳባቸውን ይዞ መጥቶ በመስራቹ ጉባኤ ተሳትፎ በ አመራርም ተመርጦ ነበር ።

ኢሕአፓን በምስረታው ደረጃም ውሸት የሚነዙበትና የሚዘምቱበትም ቀጥለውም ድርጅቱ ብሄረሰቦችን ይገንጠሉ ብሎ ግንጠላን አስተማረ አቀነቀነ በሚል እጅ እጅ ያለ ክሳቸውን ዛሬም ሲደግሙ ይደመጣሉ ። ለሶማሊያ ዚያድ ባሬም ሙሉ ድጋፍን ሰጥቶ የደርግን ጦር ከጀርባ ወግቶና ሻጥሮ አዳክሞ ለሶማሊያ ወረራ ድጋፍ ሰጠ ሲል አረመኔው መንግስቱ የለፈፈውን ዛሬም ሀቅ ብለው ለአዲሱ ትውልድ ሊያሳልፉ የሚምክሩ ቀይ ሽብርተኞች ብዙ ናቸው ። ሀቁን ግን ኢሕአፓ ሲናገር ሲያስረዳ ዓመታት አልፈዋል ። የሀሰት ዕድሜ በሀቅ አለሁ ማለት ያጥራልና በአሁኑ ጊዜ ክሱ ውድቅ መሆኑን እንዲገነጠሉ ተገፋፉ የሚባሉት ራሳቸው እያስረዱ ነው ። የኤርትራን መገንጠል ወይም ቅኝ ግዛት ናትና ነጻነት ብለው የጀብሀ አማጽያን በካይሮና ባርካ ሲነሱ ኢሕአፓ ሆነ ተራማጁ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ገና ብቅ አላሉም ነበር ። የእነ ዋቆ ጉቱ የባሌም አመጽ ከ ድርጅቱ ምስረታ በፊት የተከሰተ ነው። ኢሕአፓ ለሶማሊያ ቢያድርና ደጋፊ ቢሆን ኖሮማ ፤ ሲሶ የሀገር መሬት የሶማሊያ ግዛት ነው ብሎ እንደ ወያኔ ቢፈርም ኖሮ …ብሎ ማስላሰሉ ጠቃሚ ነው ። የሀገርን ሉዓላዊነት አሳልፎ አልሰጥ በማለቱ ብዙ ጉዳት እንደደረሰበትና በአንጻሩ ወያኔ 3 ሺ ክላሺን እንደተለገሰውና ዲፕሎማቲክ ፓስፖርትና ለአረብ ሀገሮች ድጋፍ የሚሆነውም ደብዳቤ እንደተጻፈለት የድርጅቱ መሪ የነበረው ግለሰብ በቅርቡ ለገበያ ባቀረበው መጽሃፍ መስክሯል ። ደርግ ያሰራጨው ክስ ሕዝብን በ ድርጅቱ ላይ ለማነሳሳትና ድርጅቱንም ለማጥቃት መሆኑ ለማንም ምስጢር አልበረም-- የሚያሳዝነው ግን ብዙ ዜጋ ሊወናበድና ሊደናገር መቻሉ ነው ። የኤርትራ ግንባር መሪዎችን ድርጅቱ ሲያገኛቸው ልዩነቱና ጠቡ ቅኝ ግዛት ነን የሚለውን አልቀበል በማለቱና ወያኔ ግን ይህን ሀቅ ብሎ በመዋጡ ነው ። ሟቹ መለስ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ ከ300 ገጽ ያላነሰ ሀሰት የጻፈውን ያስታውሷል። በቅርቡ ኢሳያስ አፈወርቂም ወያኔ ሽግግር የሚለውን ሀገር አጥፊ ሂደት ሲተች ኢሕአፓ የኤርትራን መገንጠል ወይም ነጻ መሆን ሲቃወም መቆየቱን አቅርቧል ። ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ይላል የሀገራችን ሰው ። እስከ መገንጠል የሚለውን መብት ማወቅ በመርህ ደረጃ ምን ማለት እንደሆነና ይዘቱንም መረዳት ያቃታቸው ተገንጠሉ ብሎ ኢሕአፓ ቀሰቀሰ ያሉት ከሃቁ የተጣላና የአለማወቅ ምስክር መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

የቀይ ሽብር ዘመቻ ሲነሳ ኢሕአፓ ቀድሞ ደርግ ላይ ተኩሶ ቆሰቀሰው የሚሉ ስለምን እንደሚናገሩ የማያውቁ አሊያ ወንጀላቸውን ሊደብቁ የሚጥሩ ደርጎች መሆናቸውን ደጋግመን ያጋለጥነው ነው ። በዚህ ሂደት ሆነ በነጻ እርምጃና ቤት ለቤት ፍተሻ ወዘተ ደግሞ መኢሶን የተባለው ድርጅት ሚና ምን እንደነበረው ዜጎች ሁሉ የሚያውቁት ነው። ኢሕአፓና መኢሶን የተጋጩት ኢሕአፓ የመሬት አዋጁን በመቃወሙ ነበር የሚለው ያፈጠጠ ውሸት ነው። እንዲያውም ይህንን አዋጅ በመደገፍ በአዲስ አበባ በተደረገው የተራማጆች ሰልፍ መገኘት ያልነበረባቸውና ህቡዕ የነበሩ የድርጅቱ አመራር አባሎች ተገኝተዋል ።

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

ከገጽ 10 የዞረ

ሁሉም የእኔ ውሸት ካንተ ይሻላል ፉክክር ስለገቡ ዝብርቅርቅ ያለ መረጃን ተብዬ በየፊናቸው ሃቅ ብለው ያናፍሳሉ። የውሸት አባት ደርግ ተብዬው አረመኔ ቡድን ለምሳሌ ኢሕአፓ የተመሰረተው በአሜሪካ የስለላ ድርጅትና በአረቦች የቤንዚን ገንዘብ ነው ብሎ ነበር ። እንደ ደርግ ከነበረማ ኢሕአፓ ድርቅ አምጥቶ ህዝብን ለረሃብ ዳርጎ ነበር።

በሁለቱ ድርጅቶች መሃል የነበረው ጠብ ደርግን መደገፍ ወይስ መቃወም በሚለው ዓቢይ ጉዳይ የተነሳ ነው ። ሌላው ሁሉ አማኝ አልባ ወሬና ትርፍ ልፈፋ ነው። ታሪክ ብረዛው ዛሬ ቢስፋፋም ፤ ራሳቸው መስማማትና መስመር ያቃታቸው ቡድኖች መለስ ብለው መኢሶና ኢሕአፓ መስማማት ባለመቻላቸው ተጎዱ የሚሉ ቢሆንም፤ ባይሆን ኖሮ ማለቱን ብንከጅልም ሁለቱ ድርጅቶች ሊስማሙና አብረው ሊሰሩ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም ። ኢሕአፓ ደርግን ጨቋኝ፤ የህዝብን ድል ቀማኛና ፋሺስት ብሎ ሲያወግዝ መኢሶን ደግሞ በሂስ ድጋፍ አቅዋም በስልጣን ሊያጅበው የወሰነ ነበር። ሁለቱም የመሰላቸውና ያመኑበትን አቅዋም መያዛቸው መብታቸው ቢሆንም በፖለቲካው ትግል ሂደት ብዙሀኑ ደግሞ (ዘማቾችን ጨምሮ) ኢሕአፓን መደገፋቸው የሚካድ አልሆነምና መኮንኖቹ ስልጣናቸውን ለመጠበቅ ወደ አፈና ሲያመሩ መኢሶን በማጀብና አልፎም ግንባር ቀደም ሆኖ በሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት በተባለውና በሌሎችም ተቋማት አማካኝነት ወንጀልን ፈጽሟል። ዛሬ ጥፋቱን በሰለባው በኢሕአፓ ላይ ለመጫን ጥረት አለ ። መኢሶን በቀበሌና ከፍተኛ አማካይነት የፈጸመው ግድያና ወንጀልን በተመለከተ ክርክርም የማያሻው ሕዝብ ሁሉ የሚያውቀው ጉዳይ ነው ። ጊዜ አልፏል በሚል አዲስ ታሪክ ለመጻፍ የሚደረገው ጥረት ከንቱ ነው ማለት ነው ። ያለፈውን ወደ ጎን ብንተውና ኢሕአፓ መኢሶንም ሆነ ሌሎች ጋር ባለው ዋና ጠላት (ደርግም ሆነ ወያኔ) ላይ ለመረባረብ በሚል በግንባር ሲሰለፍም ሀቁን በግርግር ለመሻር የሚደረገውን ጥረት በዝምታ ሊያልፈው የሚችል አይደለም ። ምነው ተሳስተናል ማለቱ ይህን ያህል ከበደ? ሁለቱ ድርጅቶች ሊስማሙ የሚችሉበት መድረክ አልነበረም ። ዛሬ ጸረ ወያኔ ድርጅቶችና ተለጣፊዎች ሊተቃቀፉ ይችላሉ ?

ከዚህ ቀደም ታሪክን በተመለከተ ትችት ባቀርብ እኛ ብቻ እንጂ ማንም ሊጽፍ አይችልም አይገባውም ተባለ ብለው ያማረሩ ነበሩ ። መልዕክቴ አልገባቸውም ሆኖ እንጂ ሌላ ነበር ። ማን ያውራ የነበረ በሚለው መንፈስ ታሪክን ከመጻፍ በፊት ታሪክን ማወቁ ይቅደም የሚል ነበረ ። ሃቅ ጫማዋን ገና ሳታጠልቅ ውሸት ዓለምን ይዞራል ተብሏል ። በአሁኑ ጊዘ በወያኔ ቀጥተኛና የእጅ አዙር ድጋፍ በዓመት ቢያንስ አራት ጸረ ኢሕአፓ መጽሃፍት አዋቂና ተራኪ ነን በሚሉ በ ኢትዮጵያ ይታተሙና ይሰራጫሉ ። መሰል መጽሃፍትም በዝግጅት ላይ እንዳሉ ምስጢር አይደለም ። ትግልና ሕዝብን የከዱና ለወያኔ ያደሩ ቅጥረኞችና ሰርጎገቦች መሆናቸው የተጋለጠ ደግሞ በየጊዜው ቃለመጠይቅ ለወያኔ መገናኛ ብዙሀን እየሠጡ ኢሕአፓ ላይ ሀሰትን ያሰራጫሉ--አዲሱን ትውልድ ለማደናገርም ይጥራሉ ። ወያኔ አዳናቂ ድረ ገጾችና መሰዳደቢያ መድረኮችም ግዴታቸውን እየተወጡ ናቸው። በቅርቡ ማንም በዚያ ደረጃ የማያውቀው ግለስብ የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበርኩ በሚል ወያኔን የሚያስደስት ትረካ አቅርቧል ። የሚያምኑት አይጠፉም--ለኢሕአፓ ግን ለዚህ ሁሉ ቅጥፈት ምላሽ መስጠቱ ራሱ ሌላ ስራ እየሆነ ነው ። ዝምታ ደግሞ መቀበል የሚመስላችው በመኖራቸው አልፎ አልፎ ውሸትን ማሸማቀቅ ግዴታችን ሆኖ ቀጥሏል። ድርጅት ከውስጡና ከውጭ ችግርና ቀውስ ያጋጥመዋል ብሎ መገመት መጠበቅ አስፈላጊ ነው ። ድርጅት ተዓምራዊ ስብስብ ሳይሆን ግለሰቦች የሚደራጁበት ነውና የህብረተሰቡም ቅራኔዎች ነጸብራቅ ነው ። የሚጎትተውና የሚያዳክመው ክስተት ብቅ ይልበትና ይፈታተነዋል ። በየጊዜው በድርጅቶች ላይ ከፋፋይ፤ከሀዲዎችና አንጃዎች መከሰታቸው የሚያስደነግጥ ሊሆን አይገባውም ፡፡ በተጨባጭ በኢሕአፓ ታሪክ አንጃዎች በየጊዜው ተከስተዋል ። ለምን የሚለውን በተመለከተ የተሰራጨውም ሀሰት ብዙ ነው ። ኢሕ አፓ ሲመሰረት የጉባኤው ተሳታፊዎች ተመክሮና ብስለት ገና ነበርና የድርጅት ዋና ጸሃፊ የሚለውን --ያውም የስልጣኑ ገደቡ ባልተገለጸበት ሁኔታ--መቀበሉ የሚያስከትለውን ችግር በቅጡ ባለመረዳት ወይም ባለመገንዘብ ቦታውን አጥብቆ ይፈልግ ለነበረው ለብርሃነ መስቀል ተለቀቀለት። እሱም ይህን የሀላፊነት ቦታ በ ስታሊናዊ ዕይታና ግምት በመውሰዱ ተመድቦ በነበረበት በኢሕአሠ ውስጥ በማንእለብኝነት ጓዶችን መበደሉና ዴሞክራሲያዊ አሰረርን መጣሱ በአባላት ተጋልጦ የድርጅቱ መሪዎች ከቦታው ማንሳት ብቻ ሳይሆን በኢሕአፓ ባለብዙ ስልጣን ሊቀመንበርም ሆነ ዋና ጸሃፊ እንዳይኖር ወስነው እስከዛሬም ይህን ቦታ የሚፈልጉትን ድርጅቱ እያገዳቸው በጋራ አመራር አሰራር ቀጥሎ ይገኛል ። ይህም ኢሕአፓን ከሌሎች ድርጅቶች ይለየዋል-- በተጨባጭ የድርጅቱ አንድና ብቸኛ ሊቀመንበር የለም ። ሊያፈርሱት ሊያጠቁት የሚፈልጉ ክፍሎች አንድ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ሊሰይሙለት ቢፈልጉም የጋራ አመራር ነው የኢሕአፓ መርህና ልምድ ።

በኢሕአፓ አንጃ ሆነው የተከሰቱ ግለሰቦች ከደረደሩት አያሌ ምክንያት ባሻገር ሁሉ ሃቁ አንጃው በምስጢር ከደርግ ጋር ያደረገውን ግንኙነትና ሴራ ደግሞ ድርጅቱ የደረሰበትና በአጭር የቀጨው ጉዳይ ነው። አንድ ሙሉ መጽሃፍ አንደኛውን አንጃ ስም ለማደስ ተጽፎ ወያኔ በሰፊው ቢያሰራጨውም የዚህንም ግለሰብ አሉታዊ ሚና ድርጅቱ ዘርዝሮ የሚያውቀው ነው ። ወደ አንጃነት ሁሉም ያመሩ በአምባገነንነት ወይም ፍጹም ሊቀመንበርነት ሊሰየሙ ሲፈልጉና አሊያም ከስልጣን ሊቀራመቱ ሲሉ አባላት እምቢኝ ስላሏቸው ነው ። የነ ብርሃነ መስቀል አንጃ ለደርግ እጅ ሰጥተንና ተስማምተን እንታገል ቢልም በስተጀርባ የነበረው ችግር የብርሃነ መስቀል ፍጹም ስልጣን ፈላጊነት መደናቀፉ ነበር ። ከዚያ እስከዚህ በመሀል የተከሰቱት የተለያ ማጠየቂያ ያልነበራቸው ሲሆን የመጨረሻዎቹ ደግሞ ልክ እንደ መጀመሪያዎቹ ስልጣን ለያዘው ሀይል እንበርከክ ከማለታቸው ሌላ መሪያችን ያሉት ደግሞ ተራ ተንኮል ከመሸረብ ውጪ መሪ ለመሆን ችሎታና ብቃቱም ያነሰው ቢሆንም የምለው ሁሉ ይፈጸም ህግ ይሁን ብሎ ሲወጠር አባላት ወግድ ስላሉት በውድቅት ፈርጥጦ ድርጅቱን ራሱን ለማውደም እስካሁን የሚዳክር ነው ። ግለሰቦች የስልጣን ጥም ለምን ኖራቸው ማለት አይቻልም ። የድርጅት አባል ቢባሉም በስነምግባርም መዝቀጣቸው ሊጠበቅ የሚችልም ነው ። ኢሕአፓ ደግሞ እንደ ተከዜ በክረምት ግመል በሬውን ሆነ እንጨቱን ሁሉ ማግበስበሱ አልቀረም ። ስንቶቹ ከሀዲዎ ያኔ በጥንቱ አባል ነበርን ይሉን የለ ? ድርጅት ግን ህግና ደምብ እስካለውና ይህንን የሚያስከብሩ ንቁ አባላት እስካሉ ድረስ ማንኘውንም የአንጃ ክስተት -- ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርስም--ተቋቁሞ ሊያቸንፈው እንደሚችል የኢሕአፓ ተመክሮ ያሳየ መሆኑ ግልጽ ነው ። በአንጃ አያያዝና ቅራኔ አፈታት ድርጅቱ ድክመት አላሳየም፤ ስህተትም አልፈጸመም ማለት ከቶ የሚቻል ባይሆንም በተቻለው መጠን በልዩነት አቅዋሞች ላይ አባላት እንዲወያዩና እንዲወስኑ አድርጓል ። በድርጅቱ መርህ መሰረት ደግሞ የድርጅቱ ውሳኔ የብዙሃኑ ነበርና ፤ ነውናም ጥቂት የስልጣን ጥመኞችና ጀሌዎቻቸው ፍላጎት የድርጅቱ አቅዋም ሊሆን አልቻለም፤ አይሆንምም ። የአንጃ መሪዎችን ስህተትና ወንጀልም ሸፋፍነውና ቀለም ቀባብተው ሊያቀርቡ የጣሩትና የሚጥሩት፤ መጽሃፍ የጻፉትና በወያኔም አጀህ የተባሉት ሁሉ ውጤታቸው ዜሮ ነው ። ምስክር ያለውን ማንም በሙግት አያቸንፈውምና ኢሕአፓ ደግሞ ምስክሩ ህዝብ ነው ፤ ታሪክ ነው ፤ ሀቁ ነው ። በየካቲት 66 አብዮት ሲፈነዳ የነበረን ተጨባጭ ሁኔታ ማጤን ተገቢ ነው ። ይህ ግንዛቤ ከተገኘ ለተከሰቱት ችግሮችና ቅራኔዎች ማጠየቂያዎቹን መረዳት ይቻላል። በጭፍኑ ግን ለሀገርና ለወገን የታገለና የተሰዋን ትውልድ ማውገዙ የከንቱነት ምልክት እንጂ ዕውቀት ንቃት አይደለም ። ትግልም መስዋዕትነትን ጠያቂ እንደመሆኑ መጠን የድርጅት አባላት ትግሉ በጠየቀው ቆራጥነት ታግለው ሲሰዉ ተጨረሱ አስጨረሷቸው ማለቱም እንዲሁ ድንቁርና ነው። መስዋዕት ሳይከፈልም መች ትግል ይሳካል ? በቅርቡ በዓለም አቅፍ ደረጃ እያየናቸው ያሉ ሕዝባዊ አመጾችስ ከባድ መስዋዕትነትን እየጠየቁ አይደል ? ሌላ መንገድ አለ ለለውጥ ፈላጊዎች ? ከዚህ ባሻገር ግን ማንኛውም ድርጅት በ ትግል እስከተሰማራ ድረስ ስህተት መፈጸሙ አይቀሬ ነው። ስህተቱን ላላመድገምና ላለማብዛት ንው የሚጠበቅበት ። ኢሕአፓም ስህተቶችን የረሳ ሳይሆን ይህን በተመለከተም ያኔ ገና በ1972 ግለ ሂሱን ያደረገ ነውና ባልሰራውና ባልፈጸመው ሊወቀስ የሚችል አይደለም ። ፋሺስቱን ደርግ በመታገሉም አጠፋሁ እንዲል ባይጠበቅ መልካም ይሆናል ። ዛሬም ወያኔን ባለው አቅም ሁሉ ይታገላል ። ለሰማዕት የገባው ቃል ትግሉን እስከ ድል መቀጠል ነው። የወያኔ አገዛዝም ከውድቀቱ እየተፋጠጠ መሆኑን ራሱ ወያኔ ያውቀዋል ። ይህን ውድቀት እውን ለማድረግ ደግሞ ድርጅቱ ትግሉን - መስዋዕትነትን እየከፈለ--ይቀጥላል ። የነ ጸጋዬና ሌሎች ጓዶች ሁሉ መስዋዕትነት መልዕክቱ ይህ ነው ።

ስለዚህም እንጻፍ ካልን ፤ ሀቅን እንጻፍ ከተባለ ከመጻፉ በፊት ሀቁን እንወቀው ማለት ተገቢ ይሆናል ። ኢሕአፓ የጋራ የአባላቱን ሁሉ ተመክሮና ትረካ መሰረት አድርጎ አልጻፈምና ለአውቅን ባዮች--ወንጀለኛ ነፍሰገዳዮች ሳይቀር- በር ከፍቷል ። ተጠያቂ ነው፤ ድክመቱ ሁላችንን ይመለከታል ። እርምት ሊደረግ ጥረት እየተካሄደም ነው ። በኢሕአፓ የነበሩትም ሆኑ ዛሬም የቀጠሉት ሁሉም ይስማሙበታል የምንለው አንዱ ዋነኛ ሀቅ መቸም ቢሆን መቼ ድርጅቱ የሀገር ሉአላዊነትን ለማንም አሳልፎ እንዳልሰጠ ነው ። ቢሰጥ ኖሮ--ትላንትም ዛሬም--ተጠቃሚ ሆኖ ለኢትዮጵያ አለኝታ ሳይሆን መርገምና ማፈሪያ ሆኖ በተገኘ ነበር ። ይህ አለመሆኑ የአባላቱ ክብርና ቅርስ ነው ። ታሪክ በሚገባ ሲጤንና ሲመረመር ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ አለኝታ ህኖ በመቆሙና ጸንቶ በመቆሙ መከራን እንደተቀበለ ያረጋግጣል ። ስንቶቹ (ከፕሮፌሰር አሥራት ውጪ) ለወያኔ አድረውና ተሸጠው ኢትዮጵያን ለቅርጫ ሲያቀርቡና ሸንፍላ ይደርሰን ይሆን ብለው ሲቋምጡ የኢሕአፓ ጀግኖች ግን በወያኔ እየተረሸኑ ነበር ። ማን ማን እንደሆነ ከዚህ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም ። እነ ጋይምና ሌሎቹም ሲሰዉና ደብዛቸው ሲጠፋ ዛሬ ድርጅቱ ላይ የሚጮሁት ከወያኔ ጎን ተሰልፈው አልነበረም ? ባዕዳን፤ ወያኔና ሻዕቢያ በ ድርጅቱ ላይ ተረባርበዋል--ማን ደጀንና አጋር ሆነለት ? ማንስ ሊያወግዘውና ምቱት በሏቸው ሊል ቾከለ? ኢሕአፓ ወያኔን ሊወጋ ሊታገል ሲጥርስ ከአሜሪካን እንግሊዝ ጋር ሆኖ ማን ሊያጠቃው ተነሳ ? እነማንስ ዩጋንዳን፤ የደቡብ ሱዳንን አማጽያን አስፈራሩ ? ኢአግስ ሲመሰረት ማን ሊያፈርሰው ጣር? ማን አገዘው? ረዳው? እነማንስ ከባድ ሻጥርና ጥቃት አካሄዱበት? በዚህ መንፈስ ብዙ ማለት እንችላለን፤ ይህ የቅርቡን በሚመለከት ነው። ቀደም ያለውን ደግሞ አውቅን ብለው ብዕር ያነሱት የሚያውቁት ብናኝ ሆኖ በመገኘቱ ጎበዝ እባካችሁ አደብ እንግዛ ፤ አላውቅም ማለት እኮ አያስገድልም ማለት ተገደን አለን ። እግረ መንገዳችንንም ከዋናው ትግላችን ጎን ታሪክን ላለማስበረዝ እየታገልን ነው ። በኢሕአፓ ሰንደቅ ስር ታግለው ለተሰዉትና እየታገሉም ላሉት ያለን ግዳጅ ነው ።

ይቀጥላል......

*በሳምንት ሁለት ጊዜ -ረቡዕና እሁድ- የሚተላለፉትን የፍኖተ ዴሞክራሲን ፕሮግራሞች www. Finote.org ያዳምጡ;።*

*በየሳምንቱ ቅዳሜ በ2፡00 PM የሚተላለፈውን የፍኖተ ኅብረ የኢሕአፓ ድምፅ ፕሮግራም እንዲሁም በ www. Finote.org ድረ ገጽ ማግኘት የሚቻል ሲሆን በተጨማሪ በቀጥታም ሆነ በማንኛቸውም ጊዜ 401-347-0175 በመደወል ማዳመጥ ይቻላል።*

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## *Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

የካቲት 29 ቀን 2007 ዓ.ም.
March 8, 2015

## <u>ሴቶች የነፃነት መብታቸውን ሳይጎናፀፉ ማህበራዊ እድገት ሊኖር አይችልም!</u>

በተለያየ አሰያየሞች የሚጠራውና በየአመቱ የሚዘከረው ማርች 8 ቀን. 2015 (የካቲት 29 ቀን)_አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዚሁ አመትም የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት በሚኖሩበት የፖለቲካ ምህዳር ላይ የተመረኮዙ የተለያዩ ሴት ተኮር መሪ ቃሎችን በመንደፍ እየተከበረ ይገኛል። ይህ ለተለያዩ ቀናቶች የሚዘልቀው የበአል አከባበር የሚታወሰው መግለጫ በማውጣት፡ „የት ነበርን? የት ደርሰናል? ምንስ ይቀረናል?“፡ የተሰኙ ጥያቄዎችን ለመዳሰስ የውይይት ሴሚናር በማዘጋጀት፡ ጥናታዊና ትምህርታዊ ዘገባዎችን በማቅረብ እንደሆነም በተለያዩ የዜና ተቋማትና ድረገጾች እየወጡ ያሉ ዜናዎች ያመለክታሉ። የካቲት 29 ቀን በርግጥም የፆታ እኩልነትን ለማስከበር የሚያገለግል የትግል መቀስቀሻና መልዕክትም ማስተላለፊያ ቀን ነው። የካቲት 29 አለም አቀፍ የሴቶች ቀን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎችም የማንነታቸው መገለጫ ነውና ከእህቶቻቸው ጋር በመሆን ሴት ጀግኖቻችንን በማስታወስ፣ ታሪካቸውንም በማወደስ ይፋዊና ይፋዊ ባልሆኑ ሁናቴ ባገር ቤትና በባዕድ አገር በሰላማዊ ሰልፍም በማጀብ በደመቀ ሁናቴ ያከብሩታል።

ይህ በአለም አቀፍ ደረጃ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንስቶ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባለሆኑ በርካታ የሲቪል ድርጅቶች እየተከበረ የሚገኘው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን መዘከር ከተጀመረበት ከ 1911 ዓ.ም. አመት ጀምሮ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች በበርካታ ውጣ ውረዶች የታጀቡ የትግል እንቅስቃሴዎች ተደርገው አመርቂ የሆኑ ውጤቶች የተገኙ ቢሆኑም ሕብረተሰቡ ባጠቃላይ የነፃነት መብቶችን ባለመጎናፀፉና ባለማስከበሩ አሁንም ድረስ የፆታ እኩልነት በተገቢው መንገድ አልተረጋገጠም። እንዲያውም በበርካታ ሕብረተሰብ ውስጥ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉ ሀገራት ፆታ ተኮር ከሆኑ ትንኮሳዎች አንስቶ በሴቶች የሚደርሱት በደሎች እጅግ አሳዛኝና አሰቃቂነታቸው ቀጥለው ይገኛሉ። ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር እንደ ቁጥራቸው መጠን በተለያዩ የሕብረተሰቡ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፏቸው የተገደበና ወሳኝ በሆኑ የሥልጣን አካላት በኃላፊነት የመመደብ ሁናቴ አሁንም ድረስ ለሴቶች በሩ ያልተከፈተ እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የወንድ የበላይነትን ባሰረፀ ሁናቴ እንዲያድጉ በመደረጋቸው ለነሱ በሴትና በቤተሰብ የሥራ መስክ ተገድበው እንዲቀሩ ይደረጋሉ። ይህንን ገደብ እንደምንም ተቋቁመውና ሰባብረው የራሳቸውን የኑሮ ሁናቴ ለመወሰን የሚጥሩ ጥቂት ሴቶች ቢኖሩም ሕብረተሰቡ የሚያሳድርባቸው ጫና ቀላል ባለመሆኑ እምብዛም ሊገፉበት አይቻላቸውም። የመማር ሁናቴ ተሳክቶላቸው የሥራ አለሙን በጥረታቸው ለመወጣት እድሉን ቢያገኙም ለእኩል ሥራ እኩል ደሞዝ አይከፈላቸውም። በጤና በኩል ተገቢውን እንክብካቤ ባለማግኘታቸውም ካላቻ ጋብቻ ጋር ተሳስሮ በእርግዝና ወቅት ከፅንስ ጀምሮ እስከ ወሊድ ድረስ ባለው ወቅት ሳይቀር ለሰውነት አድካሚ በሆነ ተግባር ለመሰማራት በመዳረጋቸውም ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠው ሕይወታቸው ባጭሩ የሚቀጬት የሴቶች ቁጥር በርካታ ነው። በሚደርስባቸው በደል ብቻ ሳይሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚደረጉ የርስ በርስ የጦር ግጭቶች ብቻ ሳይሆን ለም መሬታቸው ለባዕዳን እየተቸበቸበ ከቄያቸው በግዴታ ተፈናቅለው ለስደት ከሚዳረጉት ውስጥ አብዛኞዎች ሴቶችና ሕፃናቶች ናቸው። መጠለያ እስከሚያገኙበት ድረስ በስደት ጉዟቸው ወቅት የሚደርስባቸው ከጠልፎ ለባርነት መዳረግ አንስቶ፡ የአስገድዶ መድፈር ሰለባ መሆን፡ በእብሪተኞች ድብደባ ሳይቀር ሕይወታቸውን እስከማጥፋት የሚደርሱ የተለያዩ በደሎች አሳዛኝነታቸው የሚሰቀጥጡ ብቻ ሳይሆን በተለይም በሕፃናቱ ላይ የሚያሳድሩት የሕሊና ጠንቅ በቀላሉ የሚገመቱ እንዳልሆኑ የሥነምግባር ተመራማሪዎች አበክረው የሚገልፁት ነው። እጅግ አስከፊ በሆኑ የስደት ኑሮ ውስጥ የቤተሰባቸውንና የጨቅላ ልጆቻቸውን ሕይወት የማትረፍና የማቆየት ኃላፊነትና ግዴታ እየወደቀ የሚገኘው በእናቶች ላይ መሆኑ ደግሞ ሰቆቃቸውን ይበልጥ ያባብስባቸዋል። ይህን ሁሉ ተቋቁመው የመጠለያ ሰፈር ቢያገኙም የኑሮ ጭንቀታቸው ከዚሁ አያበቃም። ለበርካታ አመታት ለባዕዳን እርጥባን ተመፅዋጭነት በመዳረጋቸውም የተሟላ ኑሮ የመኖር እድሉን በአግባቡ ሳያገኙ ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል የሚለው ተስፋቸው ተሟጦ ይቀርና በመኖርና በመሞት አፋፍ ላይ ሕይወታቸው በዋዛ መባከኑን በሕሊናቸው ሲያስተውሉት መፈጠራቸውን የሚረግሙ በርካታዎች እንደሆኑ የድረሱልን አቤቱታቸው የሚያመላክተው ነው። ከሁሉ በላይ ቆሽጣቸውን የሚያሳርረው የሚደርስላቸው ወገን ማጣትና የለጋ ልጆቻቸውም የወደፊት እድል በዚሁ መልክ ቀጣይነት ኖሮት መዝለቁ ነው።

በሌላ በኩል ከዚህ ውድቀት ለመዳን እድሉን ያጋጠማቸውን ደግሞ በወያኔ አገዛዝ ዋና አቀናባሪት ለዘመናዊ ባርነት ወደ አረብ ሀገር እየተላኩና ለአስከፊ ኑሮ እየተዳረጉ ባላሰቡት፡ ባልገመቱትና ባልጠበቁት ሁናቴ በሚደርስባቸው በደልና ብዝበዛ የተነሳም ተማርረው ሕይወታቸውን በተለያዩ ዘዴዎች ለማጥፋት የተገደዱ እህቶቻችን ቁጥር በርካታ ለመሆናቸው በተለያዩ ጊዜ ይደርሱ አሁንም ድረስ የሚደርሱ አሳዛኝ ዜናዎች እንዲሁ የሚያመላክቱት ነው። ሰቆቃቸው በሌላ መልክ በአስከፊነቱ መቀጠሉ፡ ያልፍልኛልን አልመው ግና ለበረንዳ ተዳዳሪነትና ለዋልጌዎች ሰለባ መሆናቸውና ወደ ሀገር የመመለስ ተስፋቸው እየመነመነ ሄዶ እንደወጡ በባዕድ ሀገር መቅረታቸው ለአዕምሮ በሽታ የተጋለጡ እህቶቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልሄደም። ለዚህ እጥፍ ድርብ በደል፡ ሀዘንና ሰቆቃ ተጠያቂ የሆነው የወያኔ አገዛዝ ግን ብልሹነቱን ከባዕድ ጠላት ባልተናነሰ በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ለመሸፋፈን ሲዳክር ይገኛል። የኢትዮጵያ ሴቶች ለሆዳቸው ስግብግብነት የተጠናወታቸው በማስመሰል ሴቶችና ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፎች ድርሻ እንዲኖራቸው መደረጉ ለፍትሃዊ ኃብት ክፍፍል መረጋገጥ ትልቅ ማሳያ ነው እያሉ የሴት ባላሥልጣናቱ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋናዳ ሲነዙ ትንሽም አይሰቀጥጣቸውም። ስለ ሴቶች መብት አለመከበር፡ የዴሞክራሲ መብት አለመጎናፀፋቸው፡ አለ ተብሎ ስለሚነገረው የኤኮኖሚ እድገት ተቋዳሽ አለመሆናቸው፡ ድህነት እየቀነሰ ነው በሚሉበት ለባዕዳን መፅዋት እየተዳረጉ የሚገኙትም ሆነ በየጎዳናውና ጢሻው ውስጥ በካርቶኖች ተሸፍነው ለአይኖሩ ኑሮ ለመኖር የተገደዱ ሴቶችና ሕፃናት ቁጥራቸው በየጊዜው መጨመር በነሱ የፕሮፓጋናዳ ልፈፋም ሆነ የውሳኔና የስብሰባ ጋጋታ ተኖ የሚጠፉላቸው አይሆንም። ሁሌም መስተዋት ሆኖ ያጋልጣቸዋል።

በኢሕአፓ እምነት የአንድ ሕብረተሰብ እድገቱም ሆነ ማህበራዊ ሰላም ማስገኘት አለማስገኘቱ የሚመዘነው ለዜጎቹ በተለይም ለፆታ እኩልነት በሚሰጠው ከፍተኛ ግምትና ልዩ ትኩረት ነው እንጂ በሌላ ሊሆን አይችልም። የፆታ እኩልነት በሁለመናው መልኩ ተከብሮና በዘላቂነት እንክብካቤ ማግኘት ለሕብረተሰቡ ዘላቂ እድገት መገኘት ዋና መሰረት ነው። የኢሕአፓ የትግሉ አልፋና ኦሜጋም ይኸው ነው። ሴቶች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እስከ እለተሞታቸው ደረስ ከፆታ ትንኮስና ኃይል ከተሞላበት ኢሰብአዊ ድርጊቶች ነፃ ሆነው ለመኖር እንዲችሉ ማድረግ እንደ ኢሕአፓ ለመሰሉ ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ ለሆኑ ዜጎች ሁሉ ኃላፊነትና ግዴታ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን። ይህ ግን ላለፉት 24 አመታት በወያኔ አገዛዝ ሥር ለምትማቅቀው ኢትዮጵያ የሕልም እንጀራ እንደሆነ ይገኛል። በመሆኑም አለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስንዘክር ሴቶቻችን ሰብአዊነታቸው ሙሉዕ እንዲሆን ነፃነታቸውን በቅድሚያ መጎናፀፍና መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል። ለዚህ ስኬታማነት ኢሕአፓ ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም በቀጣይነት የበኩሉን ለማበርከት አበክሮም እንቅስቃሴውን ቀጥሎ ይገኛል።

ከዚህ አንፃር ሴቶች በራሳቸው ጥረት መደራጀትና ተደራጅቶም የወያኔን አገዛዝ ከሥልጣን ማስወገድ የመጀመሪያው ተግባር በመሆኑ በዛሬው እለት ተበክሮ መገለፅ ያለበት መሰረታዊ መልዕክት ነው። ይህ ስኬታማ እንዳይሆን የወያኔ አገዛዝ ጋሬጣ ሆኖባቸው ይገኛል። በአገዛዙ ተቀጥያነት እንጂ ሴቶች በራሳቸው ነፃነታቸውን በሚያስከብር ሁናቴ ተደራጅተው መብታቸውን ለማስከበር መታገል የተለያይ ሥም እያስገኘ ለእስር፡ ለስደትና ለሞት የሚዳርግበት ሁናቴ ላይ እንገኛለን። ይህ መቆም አለበት። ስለሆነም ለመላው አፍሪካና ጥቁር ሕዝብ በአርአያነት የሚታይ የጀግንነት ተግባር ሰርተው ለማለፍ የቻሉ እቴጌ ጣይቱን ብቻ ሳይሆን አያሌ ጀግና ሴቶችን በአድዋው 119ኛውን የድል አመት በኩራት በምንዘክርበት በአሁኑ ወቅት ለሴቶች መብት መከበርና ለነፃነታቸው መጎናፀፍ ሲሉ ባለፉት 40 ና 50 አመታት ውስጥ በተደረጉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የጀግና ታሪክ ሰርተው ያለፉ እንደ ድላይ ጃሚላ፡ ሃርነት ፅጌ፡ ወይንሸት ቆንጂትና ለሌሎችም በያሉበት እቅፍ የአበባ ጉንጉን በሕሊናችን በማቅረብና በማስታወስ ነው። በመሆኑም በዛሬው እለት በከፍተኛ ድምፅ „የሴቶች ትግል ይለምልም!“ እንላለን። ታሪካችሁ ለዘላለም ይታወስ እያልን ማስተጋባቱንም እንቀጥልበታለን።

ያለ ሴቶች ሙሉ ተሳትፎና ነፃነት መጎናፀፍ ሕዝባዊ ድል አይገኝም።
ኢሕአፓ

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056 USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com
Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

EPRP
BP 30022
92276 Bois Colombes cedex